ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 143 ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## «ፀሐይ» አውሮፕላን ከ88 ዓመታት በኋላ ወደ ሀገሯ ልትመለስ ነው

ገጽ 6






## ግብርናውን

በማዘመን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሊቀይሩ የሚችሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል

ገጽ 6



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

አቶ ከበደ ዴሲሳ

## መገናኛ ብዙኃን ሀገራዊ ምክክሩን አጀንዳ አድርገው የሚሠሩትን ሥራ አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- መገናኛ ብዙኃን የሀገራዊ ምክክር ጽንሰ-ሃሳብን ከማስረጽ ጀምሮ ኮሚሽኑ እያከናወናቸው ያሉ ሥራዎችን ለሕዝቡ ተደራሽ ለማድረግ የሚሠሩትን

መገናኛ ብዙኃን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## «ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ደህንነት ይበልጥ የሚረጋገጠው ኢትዮጵያ የባሕር በር አግኝታ ስትሳተፍ ነው»

- ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ በሻህ
የቀድሞ ዲፕሎማትና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ደህንነት የበለጠ የሚጠበቀው ኢትዮጵያ የባሕር በር አግኝታ ተሳትፎ ማድረግ ስትችል እንደሆነ ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ ገለጹ።

የቀድሞ ዲፕሎማትና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ በሻህ ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ከሶማሌላንድ ጋር መፈራረሟ ለቀጣናው ያለውን ፋይዳ አስመልክተው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄና ፍላጎት በሃይማኖትም ሆነ በሞራል እንዲሁም በሌሎች የሥነ ምግባር ሕግጋት ተቀባይነት ያለውና ምክንያታዊ እንደሆነ ገልጸዋል። ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት ብትሆን ከራሷ አልፋ የሌሎችንም ጥቅም ታስጠብቃለች ብለዋል።

ኢትዮጵያ «ጉሮሮዋን ታንቃ» የባሕር በር ሳይኖራት ከ30 ዓመታት በላይ ቆይታለች ያሉት ፕሮፌሰር ብሩክ፤

«ቀይ ባሕርና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል











አቶ አስፋው ኩማ

# ፌስቲቫሉ የገበያ ትስስር ለመፍጠርና ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ለቀጣዩ ትውልድ ለማሸጋገር ይረዳል

- 15ተኛው ከተማ አቀፍ የባህል ፌስቲቫል ከጥር 24 እስከ 26 ቀን ይካሄዳል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የባህል ፌስቲቫሉ የገበያ ትስስር ለመፍጠርና ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ለቀጣዩ ትውልድ ለማሸጋገር እንደሚረዳ የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ። 15ኛው የከተማ አቀፍ የባህል ፌስቲቫል «ባህሎቻችንን ማወቅ፤ ስብራቶቻችንን መጠገን» በሚል መሪ ሃሳብ ከጥር 24 እስከ 26 ቀን 2016 ዓ.ም ሊካሄድ ነው።

በቢሮው የባህል ዘርፍ ምክትል ኃላፊ አቶ አስፋው ኩማ ፌስቲቫሉን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ ፌስቲቫሉ የገበያ ትስስር ለመፍጠር፣ ሀገር በቀል ዕውቀቶችን ለትውልድ ለማስተላለፍና የባህል ትውውቅን በማጠናከር ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

በከተማ ደረጃ የሚዘጋጀው ፌስቲቫል ሀገሪቱ ያሏትን ባሕላዊ ትውፊት ለማስተዋወቅና የዕደ ጥበብ ውጤቶችን በኢንዱስትሪ ዘርፉ ለማስገባት እንደሚያግዝ አመልክተው፤ በባህልና ቱሪዝም መስኮች የሚኖረውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማሳደግ የሚረዳ መሆኑን ተናግረዋል።

ፌስቲቫሉ የማኅበረሰቡን ማኅበራዊ መስተጋብር እንዲሁም ሥነ-ልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቱን ለማሳደግ ያለመ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የከተማውና የአካባቢው ነዋሪ እንደሚታደሙበት አቶ አስፋው ገልጸዋል።


በፌስቲቫሉ ላይ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ምግብና መጠጥ አዘገጃጀቶች፣ የመመገቢያ ቁሶች፣ የባህል ጨዋታዎች፣ የተለያዩ አለባበስና አጊያጌጦች ላይ ያተኮሩ ዝግጅቶችን እንደሚያካትት አስታውቀዋል።

በተጨማሪም በአዲስ አበባ ሙዚየም ግቢ ውስጥ ከ400 በላይ ተሳታፊዎች የሚካፈሉበት በሽክላ ሥራና በኪሮሽ ሙያ ላይ ከባለድርሻ ጋር የሚከናወን የዕደ-ጥበብ አውደርዕይና ሥልጠና እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።

የባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ዘርፎች በተለያዩ አማራጮች እየተስፋፉና ኢኮኖሚያዊ ውጤት እያስገኙ ቢመጡም ፤ የሚጠበቀውን ያክል ጥቅም ለማግኘት በትኩረት እየሠራ ነው ብለዋል።

ቢሮው ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 14 ዓመታት የባህል ፌስቲቫል በማዘጋጀት ባህሎችን ለማሳደግና ለመጠበቅ የሚያግዙ የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ መቆየቱን ገልጸው፤ ፌስቲቫሉ መጤ ባህሎችን ለመከላከል እንዲሁም ከዕደ-ጥበብ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ባለሙያዎችን መብት ለመጠበቅ፣ ለማበረታታትና ለመደገፍ ትልቅ ሚና ይኖረዋል ሲሉ ተናግረዋል።

# ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ከ746 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል



ባዩሽ ታደሰ

**መስከረም ሰይፉ**





አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ከ746 ሚሊዮን 733ሺህ ብር በላይ ገቢ መገኘቱን አዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት አስተዳደር ዳይሬክተር ባዩሽ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኤጀንሲው ቆሻሻን በአግባቡ ለመያዝና መልሶ ለመጠቀም የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። በዚህም በስድስት ወራት ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ከ 746 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል።

ኤጀንሲው ባለፉት ስድስት ወራት ማኅበረሰቡ ቆሻሻ ሀብት መሆኑን ተረድቶ በአግባቡ እንዲያስወግድ በተለያዩ መንገዶች ግንዛቤ የመፍጠር እንዲሁም የጽዳት ዘመቻ መርሐግብሮችን የማዘጋጀት ሥራ ሲሠራ መቆየቱን ገልጸዋል።

ኤጀንሲው ማኅበራትን አደራጅቶ ለመልሶ መጠቀምና የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) ለማምረት የሚሆኑ ቆሻሻዎችን ለይተው በተለያየ መንገድ ለመልሶ መጠቀም አገልግሎት እንዲያውሉ ማድረግ ችሏል ብለዋል።

ማኅበረሰቡ ቆሻሻን በአግባቡ የመያዝ ልማዱ በየጊዜው እየተሻሻለ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፤ በግማሽ ዓመቱ በማኅበራት አማካኝነት 44ሺ 665 ቶን ቆሻሻ ተሰብስቦ ለመልሶ መጠቀም አገልግሎት ማዋል መቻሉን ገልጸዋል።

ሌላኛው በየክፍለ ከተማው ተደራጅተው ኮምፖስት የሚያመርቱ 45 ማኅበራት መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በእነዚህ ማኅበራት አንድ ሺህ 500 ቶን ኮምፖስት ለማምረት ታቅዶ አንድ ሺህ 733 ቶን ኮምፖስት በማምረት ለአገልግሎት እንዲውል መደረጉን ተናግረዋል።

በዚህም በግማሽ ዓመቱ በመልሶ መጠቀምና ኮምፖስት በማምረት ላይ የተሰማሩ ማኅበራት 746 ሚሊዮን 733ሺ 19 ብር ገቢ ማግኘታቸውን ገልጸው፤ በመልሶ መጠቀምና ኡደት ዘርፍም ከ480 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ገልጸዋል።

በመልሶ መጠቀም የሚመረቱ ቁሳቁሶችና የሚመረተው ኮምፖስት ከሌሎች ተቋማት ጋር በመነጋገር የገበያ ትስስር መፍጠር በመቻሉ ማኅበራት በትኩረት እንዲሠሩ እንዳስቻላቸውና ዘርፉ በየጊዜው የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖረው ግብአት መሆኑ አንስተዋል።

የተሰበሰበው ቆሻሻና የተገኘው ገቢም አምና ከተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸርም ጭማሪ መኖሩን አንስተዋል።

ዳይሬክተሯ ቆሻሻን በመልሶ መጠቀም ላይ ማኅበረሰቡ ያለው ግንዛቤ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም ሙሉ በሙሉ ችግሩ ተቀርፏል የሚያስብል ባለመሆኑ ግንዛቤ የመፍጠርና በአግባቡ ቆሻሻን የማያስወግዱና አምስት ራዲየስ ዙሪያቸውን የማያጸዱ አካላት ላይ ሕጋዊ ርምጃ እየወሰደ መሆኑንም ገልጸዋል።

# ደንብ ተላልፈው በተገኙ ከ300 ሺህ በላይ ሰዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል

**መስከረም ሰይፉ**



ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ

አዲስ አበባ፡- በግማሽ ዓመቱ ደንብ ተላልፈው የተገኙ ከ300 ሺህ በላይ ሰዎች ላይ ርምጃ መውሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የ2016 በጀት ዓመት የስድስት ወር እቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ ባለሥልጣኑ ባለፉት ስድስት ወራት በከተማዋ የሚከሰቱ የደንብ መተላለፎችን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ሲሠራ መቆየቱን ገልጸው ፤ በዚህም አመርቂ የሚባል ውጤት ማየት ተችሏል ብለዋል።

በግማሽ ዓመቱ ደንብ ጥሰትን ለመቀነስ የማስተማርና የመከላከል ሥራ ቢሠራም ይህንን ተላልፈው የተገኙ ከ300 ሺህ በላይ ደንብ ተላላፊዎች ላይ አስፈላጊው ርምጃ ተወስዷል። በዚህም በከተማው ሲታዩ የነበሩ ሕገወጥ የደንብ መተላለፎችን እንዲቀንሱ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች ከ56 ሺህ 300 በላይ ሕገወጥ የጎዳና ላይ ነጋዴዎችን፣ 254 ሺህ 255 ሕገ ወጥ ማስታወቂያዎች እንዲሁም 3 ሺህ 700 ሕገወጥ ግንባታዎችን ሲከውኑ የተገኙ ሰዎች ላይ ርምጃ መውሰድ መቻሉን ሻለቃ ዘሪሁን ጠቅሰዋል።

ከእነዚህና በሌሎች ደንብ ጥሰቶች በተወሰደ ርምጃም ባለሥልጣኑ ከ18 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ሥራ አስኪያጁ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የሥልጠናና ቅድም መከላከል ዘርፍ ኃላፊና ምክትል ሥራ አስኪያጅ አበባ እሸቴ በበኩላቸው፤ ባለሥልጣኑ የደንብ መተላለፍን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የተለያዩ ሥራዎች ሲሠራ ቆይቷል ብለዋል።

በዚህም ባለፉት ስድስት ወራት አራት ሺህ በጎ ፍቃደኛ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችንና ከአንድ ሺህ 700 በላይ አዳዲስ ኦፊሰሮችን ወታደራዊና የአቅም ግንባታ ሥልጠና ሰጥቶ ወደ ሥራ ማስገባቱን ገልጸዋል።

ምክትል ሥራ አስኪያጇ ከተማዋ ለነዋሪዎቹ ምቹና የደንብ መተላለፍ የቀነሰባት እንድትሆን የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። ለዚህም የመሬት ወረራ፣ የጎዳና ላይ ንግድ እንዲሁም ሌሎች ደንብ መተላለፎች መቀነሳቸው ማሳያ ነው ብለዋል።

በተለይም ወደ መሬት ባንክ የገቡ መሬቶችን የሀገርና የሕዝብ ሀብት እንደመሆናቸው በልዩ ትኩረት በመጠበቅ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ መሬት ወረራን እንዳይፈጸም ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል።



አቶ አካለወልድ አድማሱ

# ሞሃ የለስላሳ መጠጦች
## 45ኛው የሚድሮክ ግሩፕ ድርጅት ሆኖ ምርቶቹን ያቀርባል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ሞሃ የለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ 45ኛው የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ አባል ድርጅት ሆኖ ምርቶቹን ለገበያ እንዲያቀርብ ስምምነት መደረጉን ተገለጸ።

በ2016 በጀት ዓመት 55 ሚሊዮን ካሳ ፔፕሲና ሌሎች የለስላሳ መጠጦችን ለማምረት ማቀዱን ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ አስታወቀ።

ምርታቸው ተቋርጦ የነበረው ፔፕሲና በስሩ የሚገኙ ሌሎች የለስላሳ መጠጦች ወደ ምርት ሂደት መመለሳቸውን አስመልክቶ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ትናንት መግለጫ ሰጥቷል።

በሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አካለወልድ አድማሱ፤ ሞሃ የለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ ባለፉት ዓመታት የራሱ ሥራ አስፈጻሚ ያለውና ሥራዎቹን አሜሪካ ለሚገኘው ዋናው ኩባንያ ሪፖርት ሲያደርግ እንደነበር አመልክተው፤ በቅርቡ የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ አካል እንዲሆን ከኩባንያው ጋር ስምምነት መደረጉን ገልጸዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በስድስት ዘርፍ 44 ድርጅቶችን የሚያስተዳደር ሲሆን ሞሃ የለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ 45ኛው ድርጅት እንደሚሆን አስረድተዋል።

ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን በማከናወን የመዋቅርና የአሠራር ለውጥ ያደረገ ሲሆን፤ ነባራዊ ችግሩን ለመቅረፍ የአስተዳደር አካላት ለውጥ መደረጉንም አስረድተዋል።

ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደተናገሩት፤ ከዚህ በፊት በምርት ሂደቱ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመቅረፍ የማምረት ሂደቱ ሳይቆራረጥ እንዲቀጥል የሚሠራ ሲሆን፤ አሜሪካ የሚገኘው ዋናው ኩባንያም በቅርበት ድጋፎችን ያደርጋል።

ድርጅቱ መዛወሩን ተከትሎ የመዋቅር ለውጡን ተከትሎ ከሠራተኞች ጋር ተያይዞ አስፈላጊ የማሻሻያ ተግባራትን የሚያደርግ ሲሆን፤ ነባር ሠራተኞች አብረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል ብለዋል።

በሞሃ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ ሲመረቱ የነበሩ ፔፕሲና ሌሎች የለስላሳ መጠጦች ተመልሰው ወደ ምርት ሂደት መግባታቸውን አመልክተዋል።

የማምረት ተግባሩ ላለፉት አራት ወራት ተቋርጦ እንደነበር አስታውሰው፤ ለምርት መቋረጡ የአስተዳደር ችግር ዋና ምክንያት መሆኑን ጠቁመዋል።

በተጨማሪ ምርቱን በማሰራጨት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትና ሠራተኞች ጋር በጋራ የሚሠራ መሆኑን አንስተዋል።

ኢንዱስትሪው ከኪሳራ ለመውጣት የሚያስችል ስትራቴጂ ባለመኖሩ ላለፉት ዓመታት በኪሳራ ውስጥ እንደነበር ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ከሚገኙት የድርጅቱ ስምንት ፋብሪካዎች መካከል በአምስቱ የለስላሳ መጠጦችን የማምረት ሥራ ተጀምሯል ብለዋል።

ወደ ማምረት ሂደቱ መግባቱን ተከትሎ በተያዘው በጀት ዓመት 55 ሚሊዮን ካሳ የለስላሳ ምርት ለማምረት እቅድ መያዙን ገልጸዋል።

ከሚያመርታቸው የለስላሳ መጠጦች በተጨማሪ ሌሎች የመጠጥ ዓይነቶችን ለማምረት በጥናት ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

# በ22 ነጥብ 77 ቢሊዮን ብር ወጪ የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች ተከናውነዋል

**ማህሌት ብዙነህ**



77 ቢሊዮን ብር ወጪ የመንገድ ግንባታ እና ጥገኛ ሥራዎች እንደተከናወኑ ገልጸዋል።

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ በ22 ነጥብ 77 ቢሊዮን ብር ወጪ ከ4 ሺህ 700 ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች መከናወኑን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የፕላንና ፕሮግራም ማኔጅመንት ዳይሬክተር ወይዘሮ ቆንጂት ዓለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በግማሽ ዓመት 4 ሺህ 798 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች ተከናውነዋል።

በ2016 በጀት ዓመት 945 ኪሎ ሜትር አዲስ መንገድ ለመገንባት የታቀደ መሆኑን ገልጸው፤ በግማሽ ዓመት 402 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 279 ኪሎ ሜትር አዲስ መንገድ መገንባቱን አስታውቀዋል።

በዚህም የፌዴራል መንገዶችን ሽፋን በ2015 ከነበረበት 30 ሺህ 348 ኪሎ ሜትር ወደ 30 ሺህ 456 ኪሎ ሜትር ማድረስ ተችሏል ነው ያሉት።

በተጨማሪም በግማሽ ዓመት በአጠቃላይ 6 ሺህ 786 ኪሎ ሜትር መንገድ የከባድ ጥገና፣ ወቅታዊ ጥገናና መደበኛ ጥገና ለማድረግ ታቅዶ እንደነበር ጠቅሰው፤ 4 ሺህ 519 ኪሎ ሜትር መንገድ መጠገኑን ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

በግማሽ ዓመት ጥገና ከተደረገላቸው መንገዶች 85 ኪሎ ሜትሩ ከባድ ጥገና የተደረገ መሆኑን አውስተው፤ አራት ሺህ 434 ኪሎ ሜትሩ የወቅታዊና መደበኛ ጥገና የተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

101 ኪሎ ሜትር የነባር መንገዶች ማጠናከር እና የነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል ሥራ የተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ 95 ኪሎ ሜትር የሚሆነው ነባር መንገድ ደረጃ ማሻሻል መሠራቱን ተናግረዋል።

በግማሽ ዓመቱም 535 የዋና መንገድ ሥራዎችን ለመሥራት ታቅዶ 380 መፈጸም ተችሏል። በዚህም የእቅዱን 71 በመቶ መከናወኑን ወይዘሮ ቆንጂት አስታውቀዋል።

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ በ22 ነጥብ

እንደ ወይዘሮ ቆንጂት ገለጻ፤ በሀገሪቱ ያለው የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት በተፈለገው ልክ የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራ መሥራት አልተቻለም። በጸጥታ ምክንያትም 52 ፕሮጀክቶች በጊዜያዊነት 32 ፕሮጀክቶች በቋሚነት ተቋርጠዋል።

ካለው የጸጥታ ሁኔታ በተጨማሪም የግብአት እጥረት፣ የወሰን ማስከበር እና ግብአት ከቦታ ወደቦታ ለማንቀሳቀስ አስቸጋሪ በመሆኑ ሥራዎችን በበቂ ሁኔታ ለመተግበር ተግዳሮት እንደሆኑ አስታውቀው፤ ችግሩን ለመፍታትም ከግብአት አቅራቢዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ያለው ተግዳሮት ከተፈታም በቀጣይ ከ80 በመቶ በላይ አፈጻጸም ደርሰው የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ እንደሚሠራም ወይዘሮ ቆንጂት አስታውቀዋል።

# ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ ከቡና ይበልጥ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድል ይፈጥራል

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፍ የቡና ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ እንደ ቡና አምራች ሀገር ይበልጥ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድል ይፈጥራል ሲል የኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ። ከ800 በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ዓለም አቀፍ የቡና ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽን በቀጣዩ ሳምንት በሚሊኒየም አዳራሽ ሊከፈት ነው።

የቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ ከ800 በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች የሚሳተፉበት የመጀመሪያው «የአፍሪካ የቡና ሳምንት በኢትዮጵያ» እና 20ኛው የአፍሪካ ኮፊ አሶሴሽን ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽን ከጥር 28 እስከ የካቲት 2 ቀን 2016 ዓ.ም. በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል።

«ኢትዮጵያ አረንጓዴውን ወርቅ ለዓለም ያበረከተች የቡና መገኛና አምራች ሀገር ብትሆንም ከምርትና ምርታማነት ሂደቱ ጋር በተያያዘ እያገኘች ያለችው ጥቅም የሚገባትን ያህል አይደለም» ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህ መቀየር ስላለበት እንደ ሀገር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር በግሉ ዘርፍና በመንግሥት ትብብር በዓይነቱ ለየት ያለ ትልቅ ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽን አዘጋጅተናል ብለዋል።

ለአንድ ሳምንት በሚቆየው ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽን የ25 ቡና ላኪ አፍሪካ ሀገራትና የቡና ገዢ ሀገራት የግብርና ሚኒስትሮች፣ ዓለም አቀፍ የቡና ላኪዎችና ገዥዎች እንዲሁም ምሁራንና ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እንደሚታደሙ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ሀገር መሆኗንና የቡና ሀብቷን የምታስተዋውቅበት ነው። ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት የገበያ አድማሳችንን ለማስፋትና ምርትና ምርታማነታችንን ይበልጥ ለማስተዋወቅ ይረዳናል። አርሶ አደሮች ከቡና ገዢዎች፣ ቆይዎችና ተጠቃሚዎች ጋር የገበያ ትስስር ፈጥረው ምርቶቻቸውን በቀጥታ ወደ ውጭ መላክ የሚችሉበትን ዕድል ይፈጥራል ብለዋል።

ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ እንደ ቡና አምራች ሀገር እጅግ በጣም ተጠቃሚ የምትሆንበት ይሆናል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ «በተለይም የገበያ አድማሳችንን በማስፋት አፍሪካ ውስጥ ምርቶቻችንን መሸጥ የምንችልበትን ዕድል ለመፍጠር የምንችልበት ነው» ብለዋል።

"Specialty Coffee at Origin" በሚል መሪ መልዕክት በሚካሄደው ኮንፍረንስና ኤግዚቢሽን ድርጅቶች ምርታቸውን እንደሚያስተዋውቁ፤ ዝርዝር ጥናቶች ቀርበው ውይይት እንደሚደረግባቸው




አዱኛ ደበላ (ዶ/ር)

እና በሲዳማና በኦሮሚያ ክልሎች የሚገኙ ቡና አምራች አካባቢዎች በተሳታፊዎች እንደሚጎበኙ አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## እሳቤው አፍሪካዊ ወንድማማችነትን ወደ ላቀ ደረጃ ማሻገር የሚያስችል ነው!

የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ለረጅም ዓመታት ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ በሆኑ ችግሮች በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ያልተገባ ዋጋ በመክፈል ለማለፍ የተገደዱ፤ ዛሬም ቢሆን እስከ ችግሮቻቸው፣ ነገዎቻቸውን ተስፋ አድርገው ለመጠበቅ በተመሳሳይ ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

አካባቢው ካለው ጂኦ - ፖለቲካል ስትራቴጂ እና የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ በፈጠራቸው ተግዳሮቶች፤ በአካባቢው የሚገኙ ሕዝቦች ካላቸው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ የጠበቀ መስተጋብር አንጻር የሚጠበቀውን ያህል አንድነት ፈጥረው ለጋራ ፍላጎታቸው በጋራ መንቀሳቀስ ሳይችሉ ቀርተዋል።

ከዚህ ይልቅ ቀጣናውን ተሻግረው በሚመጡ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት እና ፍላጎቶቹ በፈጠሯቸው ሴራዎች፤ አካባቢው የግጭት ማዕከል ሆኗል። ሌላው ቀርቶ ተፈጥሮ ያደለቻቸውን ጸጋዎች አውቀውና አልምተው ድህነትንና ኋላ ቀርነትን መሻገር ሳይቻላቸው ቀርቷል።

የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ እና አስተሳሰቡ የወለደው የልዩነት ትርክት፤ በብዙ መልኩ ተመሳሳይ የሆነውን ሕዝብ፤ ስለ ራሱ ዕጣ ፈንታ ቁጭ ብሎ እንዳይነጋገር፤ ተነጋግሮ እንዳይግባባ፤ ተግባብቶ ለዘለቄታው ችግሮቹን በጋራ መቋቋም እና መሻገር የሚያስችል አቅም እንዳያዳብር አድርጎታል።

ይህም ቀጣናው ካለው ጂኦ ፖለቲካል ስትራቴጂክ ጠቀሜታ በተጨማሪ የብዙ የተፈጥሮ ጸጎች ባለቤት እየሆነ ባለበት ሁኔታ የድህነትና የኋላቀርነት ማሳያ ተደርጎ ተወስዷል። ከሁሉም በላይ በአካባቢው የሚገኘው የአርብቶ አደር ማኅበረሰብ የችግሩ ዋነኛ ገፈት ቀማሽ ሆኗል።

የአካባቢው አርብቶ አደሩ ማኅበረሰብ የመልማት ፍላጎትም በብዙ ተግዳሮቶች ምክንያት እውን አለመሆን፤ ማኅበረሰቡ ዛሬም ለእንስሳቱ ውሃና ግጦሽ ለማግኘት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ እየተንቀሳቀሰ እንዲኖር አስገድዶታል። ይህ ደግሞ እንደ ድርቅ ያሉ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ አደጋው የሚፈጥረው ጥፋት ሕይወትን አንድ ብሎ እንዲጀምር እስከ ማድረግ የሚደርስ ነው፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚኖረው ኑሮ ነገን በተስፋ መጠበቅ የሚያስችል አቅም የተላበሰ አይደለም። መጪዎችን ትውልዶች አስቦ ለተሻሉ ነገዎች በተስፋ መትጋት የሚያስችል መነቃቃት የሚፈጥርም አይደለም።

የዚህ አካባቢያዊ ችግር በዋናነት የተፈጥሮ ሀብት፣ የሰው ሀብት ወይም የኢንቨስትመንት ችግር አይደለም። ከዚህ ይልቅ ለጋራ ዕድገትና ተጠቃሚነት በጋራ ማሰብ የሚያስችል እሳቤ አለመኖር ነው። ዕጣ ፈንታን በጋራ መሥራት የሚያስችል መናበብ መፍጠር አለመቻልም ነው።

ይህ በቅኝ ግዛት እሳቤ ምክንያት የተፈጠረ ክፍተት፤ በቅኝ ግዛት ዘመን እንደሆነው ሁሉ የአካባቢው ሕዝቦች በአንድም ይሁን በሌላ የሀብታቸው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። የሀብት ችግር ሳይኖርባቸው የቅኝ ገዥዎቻቸውን ዳረጎት እንዲጠብቁና በእነሱ በጎ ፈቃድ እንዲኖሩ እያስገደዳቸው ነው።

በብዙ መስዋዕትነት፤ ውድ ሕይወታቸውን ገብረው ያገኙት የፖለቲካ ነፃነት፤ ባልተገባ ልዩነት በሚፈጠር ጠላትነት የቅኝ ገዥዎቻቸው የኢኮኖሚ ባርያ በመሆን፤ ነፃነታቸው ሙሉ ትርጉም እንዳይኖረው ሆኗል። በዚህም ዛሬም ቀና ብለው የሚሄዱበትን ልብ መፍጠር ተስኗቸዋል።

የቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች ከዚህ ያልተገባ የልዩነት ትርክት ከፈጠረው መከፋፋል እና መከፋፈሉ ከፈጠረው አለመተማመን፣ አለመተማመኑ ከፈጠረው ጥርጣሬ ወጥተው፤ ነገዎቻቸውን በእጆቻቸው ባሉ መልካም ዕድሎች ብሩህ ለማድረግ ዛሬ ላይ ቆም ብለው በሰከነ መንፈስ ለጋራ ተጠቃሚነት ማሰብ ይጠበቅባቸዋል።

አካባቢው ያለውን ሰፊ የውሃ ሀብት፣ የሚታረስ መሬት፣ ተስማሚ የአየር ሁኔታ፣ ማዕድናት፣ የባሕር ወደቦች ...ወዘተ ሀብቶች አቀናጅተው ቀጣናውን አዲስ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ አቅም ሆኖ መውጣት ወደሚያስችል የታሪክ ምዕራፍ ማሸጋገር ይኖርባቸዋል።

ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የጀመረችው አካባቢያዊ ጸጋዎችን አቀናጅቶ በጋራ የማደግ አስተሳሰብ እንደ መልካም አጋጣሚ ሊወስድ የሚገባው ነው ፤ አስተሳሰቡ ዘመኑን የሚዋጅ፤ በፓን አፍሪካኒዝም እሳቤ የተቃኘና አፍሪካዊ ወንድማማችነትን ወደ ላቀ ደረጃ ማሻገር የሚያስችል ነው፡፡

የአካባቢው ሀገራት ከመጡበት የችግር መንገድ፤ መንገዱ እስከዛሬ እያስከፈላቸው ካለው ያልተገባ ዋጋ አንፃር፤ አንድነታቸውን በማጠናከር ፤ ነገዎቻቸውን በጋራ ብሩህ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ በእጃቸው ያለ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን ትልቁ አቅማቸው ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የባሕር በር ስተሳሰጠ የወጪና ገቢ ንግድ

ክብረአብ በላቸው

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባሕር ሕግ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ካለው ባሕር የተፈጥሮ ሀብት እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ይህም፣ ዓሣ ማጥመድን እና በባሕር ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ፍለጋን ጨምሮ ሌሎች ከባሕር ተፈጥሮ ሀብት ጋር የተያያዙ ሀብቶች ተጠቃሚነት መብትን ያካትታል።

የዚሁ ሕግ አንቀጽ 125 ንዑስ አንቀጽ አንድ፤ የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ያለውን ባሕር የመጠቀም እና የመሸጋገር ዓለም አቀፍ መብት አላቸው። ይህ መብት የባሕር በር በሌለው ሀገር፣ የባሕር በር ባለቤት በሆነው ሀገር እና በቀጣናው መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊፈጸም እንደሚገባ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ላይ ተመላክቷል።

አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ ደግሞ፤ እነዚህ የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት በስምምነት ከተደረገ የተለየ የአገልግሎት ክፍያ ከሌለ በስተቀር ለተገለገሉበት ባሕር ምንም ዓይነት የትራፊክ ታክስ ወይንም ሌላ ክፍያ እንደማይጠየቁ ይደነግጋል።

የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በምስረታ ቻርተሩ መግቢያ ላይ ፤ በባሕር ሕግ ጉዳዮች ላይ ባሰፈረው ሀተታ የአፍሪካ ሀገራት የባሕር በር ያላቸውን ጨምሮ ከባሕር ሊያገኙት የሚገባቸውን ጥቅም እያገኙ እንዳልሆነ ያመለክታል፣ የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት ከባሕር የመጠቀም መብታቸው ሊጠበቅ እንደሚገባ እና ይህም ከዓለም አቀፍ መርህ አንጻር ሊታይ እንደሚገባ ይደነግጋል።

ከእነዚህ ዓለም አቀፋዊ የሕግ ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከውሃ አካላት ካላት ቅርበት አንጻር፤ የባሕር በር የማግኘት መብት እንዳላጣች አመላካች ነው። ይህም ከሁሉም በላይ ሀገሪቱ የወጪ ገቢ ንግዷን በማሳለጥ፣ የጀመረችው ልማት የበለጠ ስኬታማ እንዲሆን ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው። ድንገትም እያደገ ካለው የሀገሪቱ የሕዝብ ብዛት አንጻር የወደብ ጉዳይ የህልውና ጉዳይ መሆኑ የማይቀር ይሆናል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በአምራች ዘርፉ ላይ ከተጋረጡ መሰናክሎች መካከል አንዱ የሎጂስቲክስ ሥርዓቱ በፍጥነት የተሳለጠ አለመሆኑና በዚህም ምክንያት የሚፈጠረው የዋጋ ውድነት ነው። የሎጂስቲክስ ሥርዓት ከአምራች ዘርፍ ውጤታማነት ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው። ፈጣንና ቀልጣፋ የምርት ግብዓቶችና የምርቶች ዝውውር በአምራች ዘርፉ ውጤታማነት ላይ ያለው ተጽዕኖም ቀጥተኛ ተፅዕኖ ነው።

ቀልጣፋ የሎጂስቲክስ ሥርዓት ምርት እንዲጨምር እንዲሁም የምርት ስርጭት ፈጣንና የተሳለጠ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ግብዓቶችንና ምርቶችን በፍጥነት የማያገኙ አምራቾችና ምርት አከፋፋዮች፣ በምርት ሰንሰለት ውስጥ ውጤታማ ሆነው ሊቀጥሉ አይችሉም።

ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ 40 በመቶ ድርሻ ያለው የሎጂስቲክስ ዘርፍ፣ በርካታ ውስብስብ ችግሮች አሉበት። ከእነዚህ ሰንኮፎች መካከል የጭነት ዓይነቶችንና ብዛትን የሚያስተናግድ አቅም አለመኖር፤ መርከቦች በወደቦች አካባቢ ጭነት ለማራገፍ የሚያጠፉት ጊዜና በዚያም ሳቢያ የሚፈጠረው የወደብ መጨናነቅ፤ የተጓተተ የመርከቦች ኦፕሬሽን፤ የማከማቻና የጎተራዎች እጥረት፤ የጭነት መኪኖች በወደብ፣ በኬላዎች፣ በድንበርና በጭነት ክብደት መመዘኛ ጣቢያዎች የሚያጠፉት ጊዜ መብዛት ጥቂቶቹ ናቸው።

ብሔራዊ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ እንደሚያመለክተው፣ የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ ሥርዓት የሎጂስቲክስ ሥርዓት ውጤታማነት መለኪያ በሆኑት የሎጂስቲክስ ጊዜና ወጪ መመዘኛዎች ሲመዘን በእጅጉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በትራንዚት ጊዜ፣ በዕቃዎች እና በመርከቦች የወደብ ላይ ቆይታ፣ ጭነት ከወደብ በማንሳት አቅምና በመሰል የሎጂስቲክስ የአፈጻጸም መለኪያዎች በተመሳሳይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ነው።

ይህም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ ነው። በችግሩ ውስጥ ዘርፉ የሚመራበት ሕግና ፖሊሲ፣ የተዘረጋው መሠረተ ልማት፣ ዘርፉን የሚመሩና የሚቆጣጠሩ ተቋማት አሠራር፣ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብቃት እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች የየራሳቸው ድርሻዎች አሏቸው።

**ከባሕር በር በቅርብ ርቀት ላይ እያለች የወደብ ተጠቃሚነትን የተነፈገችው ኢትዮጵያ ብዙ ዋጋ እየከፈለች እስካሁን ቆይታለች**

የዓለም ባንክ የሎጂስቲክስ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚያሳየው፤ ኢትዮጵያ በዋና ዋና የሎጂስቲክስ ክዋኔ መለኪያዎች የጉምሩክ አገልግሎት፣ መሠረተ ልማት፣ ዓለም አቀፍ ጭነት፣ የሎጂስቲክስ ብቃት፣ ክትትል እና ጭነትን በወቅቱ ማድረስ፣ ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላት ሀገር ናት። ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው ብዙ ሀገራት የሎጂስቲክስ አፈፃፀማቸው እየተሻሻለ ሲሄድ የኢትዮጵያ ግን የበለጠ ማሽቆልቆሉ ነው።

ሀገሪቱ ላለፉት ተከታታይ ዓመታት ያስመዘገበችውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ የገቢና የወጪ ዕቃዎችና የሀገር ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ በመጠንና በዓይነት በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል። በመሆኑም የሀገሪቱን የወጪ ንግድ ልማት ለመደገፍ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት መካከል አንዱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጂስቲክስ ሥርዓት መዘርጋት ነው።

ቀልጣፋ የሎጂስቲክስ ሥርዓትን እውን ለማድረግ በብዛትና በጥራት ያደገ ውጤታማ የወደብ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው። ይህ ዓይነቱ የወደብ አጠቃቀም ከላይ ለተጠቀሱት የሎጂቲክስ ሥርዓቱ ችግሮች ሁነኛ መፍትሔ ይሰጣል። በቀደመው ታሪኳ የብዙ ወደቦች ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያ፣ ባለፉት 30 ዓመታት በወደብ እጦት ምክንያት ለከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ጫና ተዳርጋለች።

ለወደብ ኪራይ ከፍተኛ ገንዘብ እያወጣች ነው፤ የጭነት አገልግሎት ሥርዓቱ ፈጣንና ቀልጣፋ ባለመሆኑ የሀገሪቱ የአምራች ዘርፍ የምርት ግብዓቶችን በሚፈለገው ፍጥነት እንዳያገኝና በሀገር ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች በአጭር ጊዜ ለዓለም ገበያ እንዳይደርሱ ትልቅ መሰናክል ሆኗል።

ከባሕር በር በቅርብ ርቀት ላይ እያለች የወደብ ተጠቃሚነትን የተነፈገችው ኢትዮጵያ ብዙ ዋጋ እየከፈለች እስካሁን ቆይታለች። የምጣኔ ሀብቷ እያደገና የሕዝብ ቁጥሯም እየጨመረ የመጣ በመሆኑ የባሕር በር ጉዳይ ለኢትዮጵያ የምርጫ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ከሆነ ሰነባብቷል። በዚሁ ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰጡት ማብራሪያ ኢትዮጵያ ከ30 ዓመታት በፊት የሁለት ወደብ ባለቤት የነበረች ቢሆንም አሁን ላይ የሕዝብ ቁጥሯና ኢኮኖሚዋ በብዙ እጥፍ አድጎ አማራጭ ወደብ የሌላት በመሆኑ መቸገሯን አንስተው ነበር።

ኢትዮጵያ ይህንን ትልቅ ችግሯን የሚያቃልልና ብሔራዊ ጥቅሟን በእጅጉ ሊያስጠብቅ የሚችለውን የመግባቢያ ስምምነት ከሶማሌ ላንድ ጋር በቅርቡ ተፈራርማለች። ይህ ስምምነት የኢትዮጵያ የአመታት ስብራት የሚጠግን ከመሆኑ ባሻገር በቀጣናው ሊኖራት የሚገባውን የኃይል ሚዛን በማስጠበቅ የሚጫወተው ሚና የጎላ ነው። ከዚህ አንፃር ሁሉም ዜጋ ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ሊንቀሳቀስ ይገባል።

ዜና


አቶ የማነ ደሳለኝ

## በመዲናዋ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ 70 በመቶ ተከናውኗል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉ ተቋማትን ለማስተሳሰር የሚያስችለው የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክት 70 በመቶ መከናወኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ የማነ ደሳለኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቢሮው በከተማው አስተዳደር ስር የሚገኙ ተቋማትን ለማስተሳሰርና የተሳለጠ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እየሠራ ነው። በዚህም የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክትን 70 በመቶ ማከናወን ተችሏል።

ቢሮው በከተማው የሚገኙ ተቋማት የቴክኖሎጂ ልማቶችን ከማሻሻልና ከመጠገን ባለፈ በቀልጣፋ ኔትዎርክ ለማስተሳሰር የሚያስችል የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታን ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በጋራ በመሆን እየተከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

ተቋማትን አስተማማኝ በሆነ እና ደህንነቱ በተጠበቀ የኔትዎርክ ዝርጋታ ማስተሳሰር ዓላማ ያለው ይህ ፕሮጀክት በስድስት ወራት ለማከናወን የታቀደ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ ሁለት ወራት ውስጥ ለማጠናቀቅ እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ስማርት ሲቲ ስትራቴጂ አካል የሆነው ይህ ፕሮጀክት በከተማ አስተዳደሩ የሚሸፈን ከ200 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ በጀት በመከናወን ላይ መሆኑን አመልክተው፤ ፕሮጀክቱ በጥናት ላይ የተመሠረተና ሁሉንም ያማከለ ነው ብለዋል።

ይህም የከተማዋን የኔትዎርክ መቆራረጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመቅረፍ ብሎም ሁሉንም ተቋማት በሙሉ አቅም ወደሥራ በማስገባት የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያሻሽልና የሚያዘምን መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም አንድ ተቋም ከአንድ ተቋም በማገናኘት የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚረዳ መሆኑን አቶ የማነ አስታውቀዋል።

የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታው ሲጠናቀቅ የከተማዋን እድገት የሚመጥንና የተሻለ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንድትሆን በማስቻል አዲስ አበባን ስማርት ከተማ የማድረግ ዓላማን የሚያሳካ ነው ብለዋል።

ጥራት እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት እና ሶፍትዌር ሥርዓት ልማት ላይ ትኩረቱን አድርጎ የሚሠራው የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፤ ፕሮጀክቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እና ግብ ለማሳካት ትልቁን ድርሻ የሚወጣ መሆኑን አስታውቀዋል።

ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑንም አቶ የማነ ገልጸዋል።

መዲናዋን ስማርት ከተማ ለማድረግ የሚሠራውን ሥራ ከዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ጋር በማቀናጀት ከፌዴራል ተቋማት ጋር በቅንጅትና በልዩ ትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

## «ፀሐይ» አውሮፕላን ከ88 ዓመታት በኋላ ወደ ሀገሯ ልትመለስ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

በጀርመናዊው ኢንጅነር ሄር ሉድዊግ ዌበር እና የኢትዮጵያ ባለሞያዎች ትብብር የተሠራችው የመጀመሪያዋ «ፀሐይ» አውሮፕላን በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የዲፕሎማሲ ጥረት ከ88 ዓመታት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ልትመለስ ነው።

ማክሰኞ ጥር 21 ቀን 2016 ዓ.ም የጣልያን መንግሥት «ፀሐይ»ን ለኢትዮጵያ መንግሥት ያስረከበበት የታሪካዊ ቀን ናት።

«ፀሐይ» በ1935 ዓ.ም ሄር ሉድዊግ ዌበር የተባለው ጀርመናዊ ኢንጂነር እና የንጉሡ ፓይለት በወቅቱ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን በኢትዮጵያ የተሠራች የመጀመሪያዋ አውሮፕላን መሆኗንና ስያሜዋም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ልጅ ልዕልት ፀሐይን ለማሰብ የተሰጠ እንደነበር ተመላክቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ላለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ከጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጂኦርጂያ ሜሎኒ ጋር አውሮፕላኗ ወደ ኢትዮጵያ ስለምትመለስበት ሁኔታ ትልቅ ጥረት እና ሰፊ ንግግር ሲያደርጉ መቆየታቸውም ተገልጿል።

ፀሐይ ባለሁለት መቀመጫ እና ሁለትዮሻዊ መቆጣጠሪያ ያላት ብሎም የባለከፍተኛ ኃይል ሞተር ባለቤት ተደርጋ የተሠራች አውሮፕላን እንደነበረችም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት መረጃ ያመላክታል።

«ፀሐይ» ኮምፓስ፣ የአብራሪ መቆጣጠሪያዎች፣ ሁለት ያለ ፍሬን ማቆሚያ የተገጠሙ የማረፊያ ሽክርክሪቶች የነበሯትም ናት።

ሞተሩ ባለሰባት ሲሊንደር ዋልተር ቪነስ ሲሆን የውሃ ማቀዝቀዣ ሥርዓት የነበረው የ115 የፈረስ ጉልበት ባለቤትም እንደነበረች በመረጃው ተጠቅሷል።«ፀሐይ» ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት በኢትዮጵያ የተሠራች ብቸኛዋ አውሮፕላን ናት።

«ፀሐይ» አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ መምጣቷ የታሪክ ስብራቶችን የመጠገን ጥረቶቻችን ማሳያ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር (ዶ/ር ) ዐቢይ አሕመድ ገልጸዋል።

የ«ፀሐይ» መመለስ በሁሉም መልኩ የኢትዮጵያን የታሪክ ስብራቶች የመጠገን ሂደት እየተሳካ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ተናግረዋል።

በ1928 ዓ.ም የተገጣጠመችው «ፀሐይ» አውሮፕላን ኢትዮጵያ በዘመኑ የነበራትን የቴክኖሎጂ ልቀትና ቅርበት የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሰው፤ እንዲህ ዓይነት ጉልህ ታሪኮችን በማስቀጠል የታሪክ ስብራቶችን በመጠገን ልዕልናዋን ማስቀጠል ይገባል ብለዋል።

በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ የኢትዮጵያን ቅርሶችና ሀብቶች በማስመለስ የኢትዮጵያን የታሪክ ስብራቶች በመጠገን እድገትና ብልጽግናዋን ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረትም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

## ግብርናውን በማዘመን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሊቀይሩ የሚችሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ካለበት ደረጃ በመቀየር ሊያስፈነጥሩ እንደሚችሉ ተስፋ የተጣለባቸው እና የጨዋታውን ሕግ የሚቀይሩ 22 የመፍትሔ ርምጃዎች ተለይተው ወደ ትግበራ መግባቱን ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ።

ትኩረቱን በሥርዓተ ምግብ ላይ ባደረገውና ትናንት በተካሄደው አውደ ጥናት የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በግብርናው ዘርፍ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ካለበት ደረጃ ሊያስፈነጥሩ የሚያስችሉ የመፍትሔ ርምጃዎች ተቀምጠዋል።

የተቀየሱት አቅጣጫዎች የኢትዮጵያን የልማት ፍላጎትና የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት የሚያግዙ፣ በተለይም ርሃብንና ድህነትን ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ የሚያስችሉ ናቸው ብለዋል።

ከእነዚህ የመፍትሔ ርምጃዎች መካከል የእርሻ ሥራን በተቀናጀና በዘመናዊ መንገድ ማካሄድ፣ የመሬት አያያዝና የባለቤትነት መብት ማስፈን፣ የእርሻና የገጠር የፋይናንስ አቅርቦት አሠራሮች እንዲለወጡ ማድረግ እንደሚገኝበት ጠቅሰዋል።

በምግብ ሥርዓት ሽግግር በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ፣ በተዛማጅ የዘርፉ ፕሮግራሞች እንዲሁም ኢንቨስትመንቱን በመደገፍ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ ሽግግር እንዲመጣ የቅርብ ክትትል እየተደረገ መሆኑንም አመልክተዋል።

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሮም ያገኙት ሽልማት የምግብ ዋስትናን ብቻ ሳይሆን ሥነ ምግብ ሥርዓት ላይ እየተደረገ ላለው ጥረት እውቅና የሠጠ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የምግብ ዋስትናን ለማስፈን በኢትዮጵያ ለተጀመረው ጥረት ትልቅ አቅም ፈጥሮ ወደ ፊት ለመጓዝ እንደሚያስችልም ነው የተናገሩት።

የጤና ሚኒስትር ዶ/ር ሊያ ታደሰ በተወካያቸው ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ በኩል ባስተላለፉት መልዕክት፤ ኢትዮጵያ እኤአ 2021 የተካሄደውን የተባበሩት መንግሥታት የምግብ ሥርዓት ጉባኤ መሠረት በማድረግ የምግብ ሥርዓት ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀቷን ተናግረዋል። ፍኖተ ካርታውን ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ ተግባራት መከናወናቸውንም ነው ያመለከቱት።

በኢትዮጵያ የሥርዓተ ምግብ ስትራቴጂ በመንደፍ በኩል የተለያዩ ሥራዎች መሠራታቸውን የጠቆሙት የጤና ሚኒስትር ዴኤታው ዶ/ር ደረጀ፤ የመርሃ ግብሩ አንዱ አካል የሆነው የሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግበራ ውጤት መገኘቱንም ነው የገለፁት።

የሕፃናት፣ የወጣቶች እና የእናቶችን ሥርዓተ ምግብ ማሻሻል ላይ ሰፊ ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል። በተለይም በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት በማድረግ ድጋፍ መስጠቱንም ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግበራን ውጤታማ በማድረግ ተግባር በ2014 ዓ.ም 59 ሺ 717 ልጆችን ከመቀንጨር መታደግ ተችሏል። ሁለት ሺ 904 ልጆችን ደግሞ ከሞት መታደግ ተችሏል።

በተመሳሳይም ጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ በ2015 ዓ.ም ባካሄደው ጥናት መሠረት 99 ሺ 080 ሕፃናትን ከመቀንጨር ለመታደግ የተቻለና ሦስት ሺህ 33 ጨቅላ ሕፃናትን ከሞት መታደግ ተችሏል። መርሃ ግብሩ ሲተገበር ከነበረበት 240 ወረዳዎች ወደ 700 እንዲሰፋ መወሰኑንም አመልክተዋል።

የምግብ አለመመጣጠን ችግሮች አሁንም ኅብረተሰብን ለጤና ችግሮች ተጋላጭ በማድረግ መቀጠሉን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከሚሞቱ ሕፃናት መካከል 50 በመቶ በላይ የሚሆኑት ያለዕድሜ ሕይወት ማለፍ ምክንያት እንደነበር አመልክተዋል።

እንደ ዶ/ር ደረጀ ገለጻ፤ የመቀንጨር ችግር በዜጎች ላይ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ይፈጥራል፣ ለአእምሯዊና አካላዊ አደጋ ያጋልጣል፣ የታዳጊዎችን የትምህርት አቀባበልንና የፈጠራ አቅምንም ይቀንሳል። በሚሰማሩበትም ብቁ፣ ውጤታማና አምራች እንዳይሆኑ ያደርጋል።

በመሆኑም የመቀንጨር ችግርን ለመቀነስ ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝና ባለፉት 20 ዓመታት በተከናወኑ ተግባራት በመቀንጨር ምክንያት የሚደርሰውን ምጣኔ መቀነሱን፣ በቅርቡ በተደረገ ጥናትም ከ50 ወደ 39 በመቶ መቀነስ መቻሉንም ነው የተናገሩት።

በመቀንጨር ችግር ምክንያት ኢትዮጵያ 16 በመቶ አጠቃላይ ሀገራዊ እድገት በማሳጣት ተጽእኖ እንደሚፈጥርም ጠቁመዋል።

መርሐ ግብሩን በጣምራ ያዘጋጁት የግብርና ሚኒስትር፣ የጤና ሚኒስትርና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ናቸው።

## «ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ደህንነት ይበልጥ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ትልቅ ሀገር ሆና ይህንን ማጣቷ አሳዛኝ መሆኑን ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት ትልቅ ትርጉም ያለው እንደሆነም ጠቅሰዋል። የባሕር በሩ የንግድ ወደቧን ለማሳደግና ወታደራዊ ኃይሏን በስፍራው ለማስቀመጥ ጉልህ ሚና ያለው እንደሆነ በመግለጽ፤ በዚህ መነሻነት ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ደኅንነት የበለጠ የሚጠበቀው ኢትዮጵያ ስትሳተፍ ነው ብለዋል። ከዚህም አልፎ በተለያየ መስክ የደከሙ ሀገራት ጥቅማቸው ሲነካ መተጋገዝ ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጠባይ እንደተለመደው ይቀጥላል ነው ያሉት።

የባሕር በር ጉዳይ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ሲጠበቅ የቆየ መሆኑን ጠቅሰው፤ ስምምነቱ በጫና ሳይሆን በፍላጎት ላይ የተመሠረተ መሆኑ እንዳስደሰታቸው ተናግረዋል።

ፖለቲካዊ ሁኔታውም በነፃ ሳይሆን በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ጠቅሰዋል። የሶማሌላንድ መንግሥት ስምምነቱን የወሰነው መክሮና አስቦበት እንደሆንም ገልጸው፤ ይህ መሆኑ ደግሞ ኢትዮጵያን ነፃ ያደርጋል ብለዋል።

«እንዴት ሆነ ብለው አቧራ የሚያስነሱት ትክክል አይደሉም። ይህን የሚያደርጉት የተዛባ መረጃ የያዙ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ናቸው» ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ፤ «ኢትዮጵያ ጉሮሮዋን ታንቃ የባሕር በር ሳይኖራት ከ30 ዓመታት በላይ ቆይታለች። ትልቅ ሀገር ሆና ይህንን ማጣቷ የሚያሳዝን ነው። አሁን ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት የሚናቅ አይደለም። እኛ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ዓይናችን እያየ ታንቀን ተይዘን ማንም ከሩቅ መጥቶ በሚጠቀምበት ባሕር የበይ ተመልካች ሆነን እንድንቆይ አድርጎናል። በዚህ ጉዳይ ከእኛ በላይ የሚቀረቀርልን ማንም የለም» ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ብሩክ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ እስከ ቻይናና ላቲን አሜሪካ የሚንቀሳቀሱ በርካታ መርከቦች ያሏት ሀገር ናት። ነገር ግን ጥበቃ የሚያደርግላቸው የለም። በስምምነቱ መሠረት ገፍቶ መሄድ ከተቻለ የእነዚህን መርከቦች እንቅስቃሴ ደህንነት ለማስጠበቅም ትልቅ አጋጣሚ ይፈጠራል።

## መገናኛ ብዙኃን ሀገራዊ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሥራ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ዴሲሳ ገለጹ።

አቶ ከበደ ዴሲሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መገናኛ ብዙኃን የሀገራዊ ምክክር ጽንሰ ሃሳብን ወደ ሕዝቡ ለማጽረስ የሚያስችሉ ሰፋፊ ሥራዎችን ሲሠሩ ቆይተዋል። በቀጣይነትም በጉዳዩ ላይ ግንዛቤን በማስጨበጥ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ እየሠራቸው ያሉ ሥራዎችን ተደራሽ በማድረግ ሕዝቡ በሂደቱ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ሥራቸውን አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል።

ባለፉት ዘመናት የተደረጉ ለውጦች በመግባባትና እርቅ ባለመታገዛቸው የምክክር ጽንሰ ሃሳብ በሀገራችን ያልተለመደ አስተሳሰብና ሥራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ አሁን የመጣው ለውጥ በወሰደው ቁርጠኝነት መግባባት ሊደረስባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ተለይተው ምክክር እንዲደረግባቸው ገለልተኛ ተቋም ተደራጅቶ ወደ ሥራ መግባቱን አውስተዋል።

መገናኛ ብዙኃንም ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለሚሠራቸው ሥራዎች ሽፋን ከመስጠት ባለፈ ጽንሰ ሃሳቡን ወደ ሕዝቡ ለማስረጽ ርብርብ ሲያደርጉ እንደነበር አስታውሰው፤ ሀገራዊ ምክክሩ ለበርካታ ሀገራዊ ችግሮች መፍትሔ ይዞ ይመጣል የሚል ተስፋ ተጥሎበታል። ምክክሩ አካታችነቱ እንዲረጋገጥና ተአማኒነቱ ከፍ እንዲል በማድረግ በኩል መገናኛ ብዙኃን ትልቅ ሚና አላቸው ነው ያሉት።

ሁሉም መገናኛ ብዙኃን ጉዳዩን ቀዳሚ አጀንዳ አድርገው አስፈላጊውን ግንዛቤ መፍጠር ሕዝቡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ በኩል ሥራቸውን አጠናክረው መቀጠል ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

የሀገራዊ ምክር ሂደት ትልቅ ሥራ የሚጠየቅና በዘመናት ሂደት ውስጥ ያልተግባባንባቸውን አጀንዳዎች ወደፊት በማምጣት መግባባት ላይ ለመድረስ የሚደረግ ሥራ መሆኑን አስታውሰው፤ የሕዝብ መገናኛ ብዙኃን ብቻ ሳይሆን የግል መገናኛ ብዙኃንም ለምክክሩ መሳካት ያላቸውን የማይተካ ሚና ተረድተው በጉዳዩ ላይ እየሠሩ ያሉትን ሥራ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ያለንበት ዘመን ከፍተኛ ፉክክር የበዛበትና ከማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ ዜናዎች በብዛት የሚፈበረኩበት መሆኑን ጠቁመው፤ ትክክለኛውን መረጃ በአግባቡ ወደ ማኅበረሰቡ በማድረስ ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ሀሰተኛ ዜናዎችን ማምከን እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

በዚህም ከሚያለያዩ ይልቅ የሚያቀራርቡ መረጃዎችን በፍጥነት ተደራሽ በማድረግ የተጣለባቸውን ከፍ ያለ ሀገራዊ ኃላፊነት ተገንዝበው መሥራት እንደሚገባቸው አመልክተዋል።

# ወቅታዊ

## ‹‹ኢትዮጵያ ያገኘችውን የባህር በር እድል ለማጣጣል የሚሞክሩ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የተዳፈሩ ያህል የሚቆጠሩ ናቸው››

አቶ ነጂብ አባራያ
የጅማ ከተማ ከንቲባ

አስቴር ኤልያስ

**የአባጂፋር መናገሻ የሆነችው ታሪካዊቷ የጅማ ከተማ፤ ኢትዮጵያ በስተምዕራብ አሉኝ ከምትላቸው ከተሞች ዋናዋ እና ደማቋ ናት። ከተማዋ ከመንግስት ስርዓት መለዋወጥ ጋር ተያይዞ አንዴ ሞቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ ቀዝቀዝ ብላ የከራረመች መሆኗ ይታወቃል። እንዲያም ሆኖ ታሪካዊት ከተማ መሆኗ ሊሸፈን የማይችል እውነታ በመሆኑ ዛሬም ድረስ ጅማ ከተማ ስትጠቀስ ቤተ መንግስታቸውን ከከተማዋ አናት ላይ የገነቡት ንጉስ አባ ጂፋርም አብረው መነሳታቸው አይቀሬ ሆኖ ቀጥሏል።**

**ከቅርብ ዓመት ጀምሮ ደግሞ የጅማን የቀድሞ ታላቅነት ለመመለስ በብዙ ሲሰራ ቆይቷል። አባራዋም ተራግፎ ድምቀቷ መታየት ጀምሯል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከተማዋ እዚህ ለመድረስና በቀጣይ እየተሰሩ ስላሉ እንቅስቃሴዋን አስመልክቶ አዲስ ዘመን የከተማዋን ከንቲባ አቶ ነጂብ አባራያ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል። መልካም ንባብ።**


ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- ጅማ ከተማ በአሁኑ ወቅት ያለችበት ሁኔታ እንዴት ይገለጻል? ባለፉት ስድስት ወራት የተሰሩ አንኳር ሰራዎችስ ምን ምን ናቸው?**

**አቶ ነጂብ፡-** ጅማ ጥንታዊ ከተሞች ከሚባሉት መካከል አንዷ ነች። በኢትዮጵያ ቀድመው ከተመሰረቱት መካከል አዲስ አበባ፣ አስመራ፣ ጅማ እንዲሁም ድሬዳዋ እንደነበሩ ይታወቃል። እነዚህ አራቱ ቀድመው በመመስረት ኢትዮጵያን የመሰረቱ ከተሞች ነበሩ። ከዚህ ጋር ተያይዞ የጅማ ስም ይነሳል። ስሟ መነሳቱ ብቻ ሳይሆን ጅማ ቀድማ የተነቃቃች በእርግጥም ተመራጭ ከተማ ተብላ የምትወሰድ በምዕራብ ኢትዮጵያ የምትገኝ ከተማ ነበረች።

በመሃል ግን በተወሰነ መልኩ የመዳከም እንዲሁም ወደኋላ የመመለስ ነገር ታይቶባት ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ "ጅማን ወደነበረ ስሟ እንመልሳት" የሚል እቅድ ያዝን፤ ለዚያ ደግሞ በመጀመሪያ ጅማ ምን አላት? የሚለውን ፈተሽን። በመጀመሪያ የተረዳነው ነገር ቢኖር ጅማ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ከተማ መሆኗን ነው። ለምሳሌ ያህል ጅማ፣ በመሃላቸው ወንዞች አቋርጠዋቸው ከሚያልፍባቸው ጥቂት ከተማዎች አንዷ ናት። በአብነት የሚጠቀሰው አዌቱ ወንዝ ወደ 12 ነጥብ አምስት ኪሎ ሜትር ርዝመት ያህል ከተማዋን አቋርጦ የሚያልፍ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ትንንሾች ወንዞች ያሉ ሲሆን፣ አንደኛው ኪቶ የሚባል ወንዝ ነው። ትንንሾቹ ወንዞች ከአዌቱ ወንዝ ጋር ተገናኝተው የግቤ ገባር ይሆናሉ፤ ግቤ ቁጥር አንድ ጅማ ከተማን ነክቶ የሚያልፍ ነው። ወንዞቹ ከግቤ ጋር ሲገናኙ ሐይቅ መፍጠር ቻሉ። እንደሚታወቀው ጅማ በተራራዎች የተከበበች ከተማ ናት። ተራራዋም ደን የለበሰ ነው። ከዚህ የተነሳ በተፈጥሮ የታደለች፣ ለምለምና አረንጓዴ ከተማ ናት።

ይህች በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ከተማ፣ ወንዞቿ ክረምት ክረምት ስለሚሞሉ ሕዝቧን ያፈናቅሉ ነበር። ሌሎችም መሰል ችግሮች ይታያሉ። ከዚህ የተነሳ የሕዝብን ችግር እንፍታ በሚል ወንዙ ሞልቶ ሕዝቡን እንዳያፈናቅል እና ንብረት እንዳይጎዳ የማድረግ ስራ ያዝን። "የሚያጋጥመውን ችግር ወደ እድል መቀየር" በሚለው የጠቅላይ ሚኒስትራችን መርህ መነሻነት አካባቢን ለማስዋብ ተነሳስተን ወደስራ ገባን። ከተማችንን መዝናኛ እና ምቹ ለምን አናደርገውም? በሚል ተነሳሽነቱን ፈጠርን። ይህ በመሆኑም የወንዝ ዳርቻ ልማት ላይ ተሰማራን። በአሁኑ ወቅት ወደ አራት ኪሎ ሜትር ገደማ ወንዙ የሚሄድበትን መንገድ ከሶስት ሜትር ወደ 20 ሜትር ማስፋት ቻልን። በአካባቢው የነበሩ ቤቶች እንዲነሱ በማድረግ የእግረኛ መንገድ እንዲሰራ እና አበባ እንዲተከል በማድረግ ለደከመው ማረፊያ እንዲሁም ማንበቢያ እንዲሆን ማድረግ ቻልን። የተለያዩ መዝናኛ ቦታዎችም ለመገንባት በቃን።

ከተማዋ የምትታወቅበት አዌቱ መናፈሻ አለ። ሌላው ደግሞ የወጣቶች ማዕከል ነው። እነዚህ ሁለቱ ሕዝብ የሚገለገልባቸው ሲሆን፣ በመሃላቸው ትልቅ መንገድ አለ። በአካባቢው ሕዝብ መተላለፍ ያስችለው ዘንድ ድልድይ እንዲሰራ የተደረገ ሲሆን፣ ድልድዩም ጅማ በሚታወቅበት የበርጩማ ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጎ የተገነባ ነው። ስራው ገና ያላለቀ ሲሆን፣ የሚገነባውም ከከተማዋ ከምንሰበስበው ገቢ ነው።

በአሁኑ ወቅት ምዕራፍ አንድና ሁለትን ጨርሰን ወደምዕራፍ ሶስት የተሸጋገርን ሲሆን፣ በ2017 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ ይታሰባል። ከእሱ ጎን ለጎን በከተማ ፓርክ ላይ እየሰራነው ያለው ስራ ተጠቃሽ ነው። ወደ 12 ነጥብ አምስት ሔክታር ስፋት ያለው በውስጡ የህጻናት ማዋያ፣ የባህል ማዕከል፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ሬስቶራንትና ሌሎች ነገሮች የሚኖሩት ይሆናል። ይህም በአሁኑ ሰዓት በጥሩ ሁኔታ እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ባለፉት ስድስት ወራት ከሰራችኋቸው ስራዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት የትኛቹ ናቸው ? ስምን ያህሉስ ወጣት የስራ እድል ማመቻቸት ተቻለ?**

**አቶ ነጂብ፡-** የሰራነው የወንዝ ዳርቻ ልማት ነው፤ ከተማዋ ንጹህ፣ ጽዱ፣ አረንጓዴና ውብ እንዲሁ ለነዋሪዎቿ ምቹ እንድትሆን በማድረግ ረገድ እየተሰሩ ካሉ ስራዎች አንዱ እና ዋነኛው ይኸው የወንዝ ዳርቻና የፓርክ ስራ ነው። በሁለተኛ ደረጃ መሰረተ ልማት ነው። በጅማ ከተማ ያለው አስፓልት መንገድ ወደአፈርነት ለመቀየር የዳዳው ነው። ስለዚህ ጅማ ከተማ መሰረተ ልማት እንደማንኛውም ከተማ ይፈልጋል። ስለዚህ ያረጀውን መሰረተ ልማት የማደስ ስራ እየሰራን ነው። በጣም የቆየ እና ወደአፈርነት የተለወጠውን የአስፓልት መንገድ እንደገና ጠርገን አንድ ኪሎ ሜትር አካባቢ እንደአዲስ ሰርተናል። ሁለት ቀበሌዎችን የሚያያይዝ ወደ አምስት ኪሎ ሜትር የአስፓልት መንገድም ሰርተናል።

ሌላው የነበሩ መንገዶችን ማስፋፋት ነው። በየመንገዱ ዳርዳር በሼድና በፕላስቲክ ተሸፍኖ የነበረውን አንስተን ወደ አራት ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው፤ በሁለቱም በኩል አምስት አምስት ሜትር ስፋት ያለው መንገድ ሰርተናል። ይህም ወደ 30 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበት በዚህ ዓመት እና ባለፈው ዓመት የተሰራ ስራ ነው። ሌላው የመብራት ዝርጋታ ሲሆን፣ እሱም በሰፊው እየተኬደበት ይገኛል። የውሃ ዝርጋታም በተመሳሳይ እየሰራን ነን።

የአስፓልት መንገዱ ወደ 400 ሚሊዮን ብር ገደማ የፈጀ ነው። የዚህ ወጪ ምንጩ የከተማ ገቢ ነው። የወንዝ ዳርቻ ልማቱም እንዲሁ እየተሰራ ያለው በከተማ ገቢ ነው። ይህም ወደ 200 ሚሊዮን ገደማ የፈጀ ሲሆን፣ ይህም በየዓመቱ 40 ሚሊዮን ብር፣ 50 ሚሊዮን ብር እየተባለ 200 ሚሊዮን ብር ላይ የተደረሰ ነው። ይህም ወደ ሶስት ዓመት ገደማ የወሰደ ተግባር ነው። የወንዝ ዳርቻ ልማት ያለው በዚህ ደረጃ ነው። ፓርኪንጉም እንዲሁ ወደ 50 ሚሊዮን ብር ያህል ወጪ ወጥቶበት እየሰራን ነው። አራት ኪሎ መንገዱ ደግሞ ወደ 30 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎ እየተሰራ ነው።

ሌላው የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አኳያ ተነሳሽነቱ በክልል ደረጃ ተቀርጾ ወርዷል። ለምሳሌ ዶሮ እርባታ ላይ በሰፊው እንዲሰራና ክላስተሮችም እየተገነቡ ሲሆን፣ በተያዘው እቅድም ወደ 300 ክላስተር ገንብተን አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶሮዎች ወደዚህ ከተማ ለማስገባት ነው። በአሁኑ ወቅት ወደ 400 ሺ ዶሮዎች መያዝ የሚችል ሼዶች አስገንብተናል።

ሌላው የወተት ልማት ነው። ወደ 67 ክላስተር ተገንብቶ ወደ አንድ ሺ 500 የሚሆኑ ምርጥ ዘር ላሞች መግባት ችለዋል። እያንዳንዱ ሼድ ለ20 ወጣቶች የስራ እድል ይፈጥራል። ወደ ስምንት ሺ የሚሆኑ ከብቶችን አደልቦ ለገበያ የሚያበቃ ማደለቢያም አለ።

የፍራፍሬ ክላስተርም በሰፊው እየተሰራበት ሲሆን፣ ንብ እርባታም አለ፤ አጠቃላይ 518 ክላስተር በከተማችን ላይ መሰራት አለበት ተብሎ ከተሰጠን ወደ 340 የሚሆን ክላስተር መስራት ተችሏል። ስራም ጀምረናል።

በዚህ ዓመት 28 ሺ ወጣቶችን ወደስራ ማስገባት አለባችሁ ተብሎ በስድስት ወር ውስጥ ወደ 20 ሺ ገደማ ወጣት ወደስራ ማስገባት ችለናል። ብዙዎቹ የምንሰራቸው ስራዎች ለወጣቶች ሲሆን፣ በዚህ ውስጥ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው የሚችል ሁሉት ነገር አለ። አንደኛው የኑሮ ውድነትን መቋቋም የሚያስችል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለወጣቱ የስራ እድል መፍጠር ነው።

በሌላ በኩል እንደፌዴራል ተይዞ እየተሰራበት ያለ "ብቃት" የሚል ፕሮግራም አለ። በሱ ፕሮግራም አንድ ሺ ያህል ወጣት እንዲሰለጥኑ ይደረጋል። ከስልጠና በኋላ ከባለሀብቶች ጋር ይጣመራሉ። ከእነርሱም ጋር ወደ ስድስት ወር ያህል እንዲቆዩ ይደረጋል። ከዚያም ራሳቸውን ችለው እንዲወጡ ይደረጋል። "ብቃት" በሚል ፕሮግራም በጎንደር፣ ሐዋሳ እና ጅማ በአብነት ተይዘው እየተሰራባቸው ያሉ ከተሞች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የከተማዋ ገቢ አሰባሰብ ምን ይመስላል?**

**አቶ ነጂብ፡-** ከተማችን ቀደም ሲል ገቢ አሰባሰቡ ላይ በጣም ደካማ ነበር። የከተማችን ገቢ ከሁለት ዓመት በፊት 400 ሚሊዮን ብር ብቻ ነበር። ባለፈው ዓመት አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተቻለ። ዘንድሮ ደግሞ ሶስት ቢሊዮን ብር እናስገባለን ብለን በግማሽ ዓመቱ ወደ አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ችለናል። ፕሮጀክቶችንም ሆነ መሰረተ ልማቶችን እየሰራን ያለነው በምንሰበስበው የከተማ ገቢ ነው።

በአሁኑ ወቅት አመራሩ አካባቢ ያለው ስሜት ቁጭት ነው። ብዙዎቹም ከተማዋን የተሻለ ቦታ ለማድረስ ይታገላሉ። ጅማ ከ100 ዓመት በፊት ተመራጭ የነበረች ከተማ ናት። በመካከል ደግሞ ይህ ሁሉ ቀርቶ ተጎሳቁላ ነበር። እንዲያውም ከተማ ሲያረጅ እንደ ጅማ ተብሎም እንደነበር ይታወሳል። አሁን ያንን የቀደመ ተፈላጊነቷንና በምዕራብ ደቡብ ዋናዋ ከተማ የሚያስብላት ሁኔታን ለመመለስ ተነሳሽነቱ ተፈጥሯል። በመጀመሪያም ያነቃቃትና ተመራጭ ከተማ እንድትሆን ያደረጋት ስርዓት ነው። መልሶም ያዳካማት ስርዓት ነው። አሁንም መልሶ እንድትነቃቃ ያደረጋት ስርዓት ነው። ስለዚህ ጅማን ቀደም ሲል ያዳካማትም ሆነ አሁን ያነቃቃት ስርዓት ነው። በአሁኑ ወቅት እኩልነትን የሚያረጋግጥ፣ ዴሞክራሲን የሚያሰፍን፣ ፌዴራሊዝምን በትክክል የሚተገብር መንግስት ተገኘ። ሕዝቡም በዚህ ደስተኛ ነው። ባለን አቅምና እድል ሰርተን መለወጥ እንችላለን፤ ጫና የለብንም የሚል ግንዛቤ ማኅበረሰቡ ዘንድ ተፈጥሯል።

**አዲስ ዘመን፡- የከተማዋ ሰላምና ጸጥታ ምን ይመስላል? ከተማዋ ለኢንቨስትመንት ያላት ምቹ ሁኔታንም አያይዘው ቢገልጹልን?**

**አቶ ነጂብ፡-** የጅማ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ነው። የጅማ ከተማ ሰው፣ የኢትዮጵያዊነት እሴትን ተላብሶ የሚኖርባት ናት። ጅማ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ጸንተው፣ ተዋደውና ተከባብረው በአንድነት የሚኖሩባት ትንሿ ኢትዮጵያ ናት። ሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰብ ያለባትና እርስ በእርስም ተዋድደውና ተከባብረው የሚኖሩባት ከተማ ነች።

አባ ጅፋርም በጊዜያቸው ለሰላም ያላቸው ቦታ ትልቅ ነው። ጠዋት ላይ ከሰዎች ጋር ሲገናኙ ቀኑን የሚጀምሩት "ቡና እና ሰላም አትጡ!" በሚል ነው። እንግዳን ሲቀበሉ፤ "ቡና ጠጡ" ብለው ሲሆን፤ ሲሸኟቸው ደግሞ ቡና ሰጥተዋቸው "ቡና እና ሰላም አይለያችሁ!" ብለው ነው። እሱ አባባላቸው ኅብረተሰቡ ውስጥ ባህል ሆኖ እስከዛሬ መዝለቅ ችሏል።

በዚህ ላይ ደግሞ የኃይማኖት አባቶች ያላቸው ስፍራ ትልቅ ነው። ጸሎታቸውንም ሆነ ዱዓቸውን ሲጀምሩ ሰላም ለሰው ልጅ ዋስትናው መሆኑን ጠንቅቀው በማወቅ ነው። ጸሎታቸውንም ዱዓቸውን የሚያደርጉ የእምነት አባቶች ሲገናኙ የሚሰብኩት አንድነትን ነው። የኦርቶዶክስ፣ የሙስሊም እና የፕሮቴስታንት ኃይማኖት መሪዎች አንድ ፕሮግራም ሲኖረን እንዲመርቁ የሚነሱት አንድ ላይ ነው። አንዱ ከቀረ እንኳ ሌሎቹ መነሳት አይፈልጉም። ምክንያቱም ለሕዝብ ሰላምና አንድነት ወሳኝ መሆኑን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ከገጽ 7 የዞረ

## ‹‹ኢትዮጵያ ያገኘችውን የባህር በር እድል ለማጣጣል...

ጠንቅቀው ያውቃሉና ነው። ከዚህ የተነሳ ሶስቱም አንድ ላይ ተጠራርተውና ተቃቅፈው ወደ መድረኩ መጥተው የዕለቱ መርሃግብር ሳይጀመር ይመርቃሉ።

በተመሳሳይ የአገር ሽማግሌውም ሆነ ወጣቱ ብሔር ከብሔር ሳይለያዩ ሰላሙን በማስጠበቅ በኩል ሚናቸውን እኩል እየተወጡ ነው። አንዱ ከሌላው አይለይም። ጅማ ከተማ እስካሁን ድረስ ሰላሟ ተጠብቆ እዚህ መድረስ የቻለችው ለዚህም ነው። አሁንም ቢሆን ከተማችን ሰላም ነው ብለን አንዘናጋም፤ ሰላማችንን ለማስጠበቅ አሁንም ሕዝባችንን ይዘን እንቀጥላለን። ከሕዝብ ጋር ስለምንሰራም የሰላሙ ጉዳይ አስተማማኝ ነው ማለት ይቻላል።

እንዲያውም በሌላ አካባቢ ያሉ ሌሎች ከተሞች ከጅማ መማር አለባቸው የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም በጅማ ከተማ ዋና ጉዳዩ በኢትዮጵያዊነት መጸናቱ ነው። በኃይማኖትና በብሔር አለመከፋፈሉ ነው። ሰላም የሁሉም መሰረት ነው ብሎ መውሰዱ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከሁሉም በላይ ለሰላም ትልቅ ቦታ ሰጥቶ መሰራቱ በመቻሉ ነው እላለሁ።

ሰላሙ አስተማማኝ ከመሆኑ የተነሳ ልማቱ እንደቀጠለ ነው። ጅማ እንደሚታወቀው የአየር ጸባዩ ጥሩ የሚባል ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ለኢንዱስትሪ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብት ያለበት ነው። ማዕድኑ፣ ቡናው እንዲሁም ፍራፍሬው አለ። እነዚህ ለኢንዱስትሪ ግብዓት ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላው ደግሞ ስንዴም በቆሎም ይመረታል። ባለሀብቶች ምንም የሚያሰጋቸው ነገር የለም። ጅማ የሰላም ከተማ ነች። ሕዝቡም ሰው ወዳድ ነው። የአገር ውስጡም ሆነ የውጭ ዜጋው ከተማችንን እንደቤቱ እና ቀዬው ማየት ይችላል። ባለሀብቶችን ስንቀበል ልክ የቤታቸው ያህል እንዲሰማቸው በማድረግ ነው። ደግሞም ያሉበት ድረስ ሔደንም እንቀበላቸዋለን እንጂ ተቀምጠን አንጠብቃቸውም። እዚህ ከተማችን መጥተው ስራ የጀመሩትን ደግሞ ለንብረታቸውም ሆነ ለደህንነታቸው ዋስትና ሊሆን የሚችለው ማኅበረሰቡ ራሱ ነው። ስለዚህም ወደከተማችን መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ማሻሻል ላይ ምን ያህል ተሰርቷል? በከተማዋ የተማሪዎች ምገባ መርሃግብርን በተመለከተስ ምን ታስባል?**

**አቶ ነጂብ፡-** ለትምህርት ጥራት ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ በሚል በመንግስት የተቀመጠ አቅጣጫ አለ። እናም እሱን መሰረት አድርገን እየሰራን ነው። የመጀመሪያው ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲገቡ አድርገናል። ተማሪዎቹ የትምህርት ሒደቱ ምቹ እንዲሆንላቸው የትምህርት ቤት ደረጃ ማሻሻል ስራ ሰርተናል። ይህ በሕዝብም ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ ሲሰራ ነበር። ወደ 30 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ወጪ ሆኖ ትምህርት ቤቶች ማሻሻል ላይ ሲሰራ ቆይቷል።

አጠቃላይ ትምህርት ቤት ማስፋፊያ እና ደረጃ ማሳደግ የወጣው ወጪ ወደ 115 ሚሊዮን ብር ነው። በዚህ ውስጥ እንደእኛ ክልል “ቡዑራ ቦሮ” የሚባል ወይም መዋዕለ ህጻናት ፕሮግራም ብለን የምንሰራው አለ። ይህንን የኦርቶዶክስ ቤተ እምነት 25 ሚሊዮን ወጪ በማድረግ ሰርቶ ሰጥቶናል፤ የሙስሊሙ እና የፕሮቴስታንት ቤተ እምነትቶች እንዲሁ እየሰሩ ነው። ባለሀብቶችም በየስራ ዘርፋቸው ተደራጅተው በመስራታቸው ወደ 19 ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ቤት ተገንብቷል። ትምህርት ቤቶቹ ሻወር እና መጸዳጃ ቤት፣ መጫወቻ እና ማረፊያ ቦታ ያለው ነው። በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

ከተማሪ ምገባ ጋር ተያይዞ ወደ 28 ሺ ተማሪዎችን መመገብ አቅደን በአሁኑ ሰዓት በ25 ትምህርት ቤት ውስጥ 26 ሺ ተማሪዎች እየተመገቡ ናቸው። የምገባ ፕሮግራሙ ሁለተኛ ዓመቱን ይዟል። ባለፈው ዓመት ስንሰራበት ቆይተናል። የተወሰኑ ክፍተቶች ነበሩ፤ እነዚያን ክፍተቶች በዚህ ዓመት አርመን አሁን አንድ ትምህርት ቤት ብቻ ሲቀር ሁሉም ትምህርት ቤት ምገባ ተጀምሯል። ጉዳዩንም በየጊዜው እየተከታተልንና እየገመገምን እንገኛለን። በመጀመሪያ ደረጃ ለምገባ ፕሮግራሙ የሚሆኑ ግብዓቶች በአይነት ተሰብስበው ማከማቻ መጋዘን አስገብተናል።

ሌላው የተማሪ ውጤትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ አመራር እንዲደገፍ በሚል ስራ እየተሰራ ነው፤ እኔ ራሴ አሁን እንድከታተለው የተሰጠኝ ትምህርት ቤት አለኝ። ይህም፣ “አባ ቡና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት” የሚባል ሲሆን፣ አንድም ተማሪ ያላሳለፈውን ትምህርት ቤት መያዝ ያለበት ከንቲባው ነው በተባለው መሰረት ይዤያለሁ። ሒደቱም እከታተላለሁ፤ ገምግሜዋለሁም። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አነስተኛ ቁጥርን ብቻ ያሳለፈውን ደግሞ እንዲይዝ የተደረገው የፓርቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ነው። እንዲሁም ምክትል ከንቲባ እያለ አምስት ስራ አስፈጻሚዎች አፈጻጸማቸው የወረደ ትምህርት ቤት ይዘው እንዲደግፉ ተደርጎ ስራ ተጀምሯል።



**ይህ የባህር በር ስምምነት የአንድ ቡድን ወይም የአንድ ፓርቲ ጉዳይ ሳይሆን የአገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ነው**

ስራው የሚሰራው ተማሪዎችን በሶስት ደረጃ በመክፈል ነው። ይኸውም ደከም ያሉ፣ መካከለኛ እና ፈጣን የሆኑ ተማሪዎች በሚል እንዲለዩ ይደረጋል። ተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን መምህራንንም ለየናቸው። በጣም ፈጣን የሆኑ መምህራንን ለብቻ አደረግን፤ መካከለኛ የሆኑትን ደግሞ እንዲሁ ለብቻ ከለየን በኋላ መምህራኑ እርስ በእርስ እንዲደጋገፉ አደረግን። በተለይም ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲፈጥሩ አመቻቸን። ይህን ካመቻቸን በኋላ ትንሽ ደከም ያሉ ተማሪዎች ተጨማሪ ሰዓት ተሰጥቷቸው እንዲደገፉ፤ በተመሳሳይ መካከለኛ የሆኑትም ድጋፍ እንዲያገኙ፤ ፈጣኖቹ ደግሞ ይበልጥ እንዲጠናከሩ የተለያዩ የመማሪያ ግብዓት እንዲሰጣቸው አደረግን።

በሌላ ደረጃ ደግሞ 12ኛ፣ 8ኛ እና 6ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች አገር አቀፍ ፈተና ወሳጆች በመሆናቸው የተለየ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት ጀመርን፤ በተለይ ለ12ኛ ክፍል በተለየ መልክ ቤተ መጽሐፍት እንዲመቻችላቸው፣ ሌሎች አስፈላጊ መጽሐፍት እንዲዘጋጅላቸው እና የቀደመው የሰባት ዓመት ዎርክሺት (አገር አቀፍ የፈተና ጥያቄዎች) እንዲቀርብላቸውና ጥያቄዎችን በመስራት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ የማድረግ ስራ ነው፤ መምህራን ደግሞ ቅዳሜ እና እሁድን ጨምሮ፤ የጠዋት ፈረቃ ከሆኑ ከሰዓት አሊያም ማታ ላይ ፕሮግራም ተይዞላቸው በደንብ እንዲሰራ አቅጣጫ አስቀመጥን።

ለምሳሌ እኔ ያለሁበት ትምህርት ቤት ሁለተኛ ደረጃ ነው፤ 12ኛ ክፍል በተለየ መልክ እንዲደገፉ 9ኛ፣ 10ኛ እና 11ኛ ደግሞ ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ፈጣን ተማሪዎች ለየብቻ እየተደገፉ ወደፊት ለፊት የሚመጡበትን ሁኔታ ፈጥረን በየጊዜው እየገመገምን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- በጅማ ከተማ ባለፉት ስድስት ወራት የተገኙ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ካሉ ቢጠቅሱልን?**

**አቶ ነጂብ፡-** ከኢንቨስትመንት ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ጅማ ላይ ትንሽ የመቀዛቀዝ ሁኔታ ታይቶ ነበር። ይሁንና ለማነቃቃት የሰራነው ስራ አለ። ካለፈው ዓመት እስካሁኑ ሰዓት ድረስ 120 የሚሆኑ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ለማሳያ ሆቴል፣ ሪል ስቴት፣ ማኑፋክቸሪንግ እና በተለያየ የስራ ዘርፍ ላይ የተሳተፉ አሉ። እነርሱም የአስራ አምስት ቢሊዮን ብር ካፒታል አስመዝግበው በከተማ ደረጃ መሬት ተለይቶ መሟላት ያለባቸው ነገሮች ታይተው የኢንቨስትመንት ኮሚቴው እንዲወስን ተደርጓል። ይህም በክልሉ የኢንቨስትመንት ቦርድ ይመራል። ከቦርዱ ጸድቆ የተመለሰው ወደ 120 ፕሮጀክት ነው። ከእነዚያ ውስጥ ወደ 94ቱ ወደስራ አስገብተናቸዋል።

ከእነዛ ውስጥ ደግሞ ጥሩ የሚባል እንቅስቃሴ ያላቸው አሉ። ለምሳሌ ኃይሌ ሪዞርት ግንባታውን በስምንት ወር ውስጥ ሊጨርስ ደርሷል። ወደ 120 መኝታ ክፍል ያለውን ሪዞርት በአሁኑ ወቅት አጠናቅቆ ቀለም በመቀባት ላይ ነው። ሴንትራል ሆቴልም ደረጃውን ወደ አምስት ኮከብ ለማሳደግ በአራትና አምስት ወራት ውስጥ የመጨረሻውን የቆርቆሮ ክዳን በማልበስ ላይ ይገኛል። ከእነዚህ ሌላ ደግሞ አጠናቅቀው ስራ የጀመሩም አሉ። ለምሳሌ ኮፊ ፕሮሰሲንግን ኤልያስ ጀበል የሚባል ባለሀብት በአራት ወራት ውስጥ ግንባታውን አጠናቅቆ፣ ማሽን ከቻይና አስገብቶ ቡናውን አንድ ጊዜ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ችሏል። ለውጭ ገበያ ያቀረበውም ወደ ሶስት ሺ ኩንታል ቡና ገደማ ነው። አሁን አሁን ከበፊቱ የተሻለ ነገር እያየን ነው። ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ወቅት መነቃቃት አለ ማለት ይቻላል። ይህ ሁሉ የሆነው በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ውስጥ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከተማዋ ለኢንቨስትመንት ምን አይነት ምቹ ሁኔታን ፈጥራለች? ምንስ አማራጮች አሏት?**

**አቶ ነጂብ፡-** ለምሳሌ መሬት ለከተማ ግብርና፣ በተመሳሳይ ለሆቴል ኢንዱስትሪ አዘጋጅተናል። እንዲሁም ለኢንዱስትሪም የተዘጋጀ መሬት አለ። በማኑፋክቸሪንግ እና በኮፊ ፕሮሰሲንግ እንዲሁም ማርን ፕሮሰስ ለሚያደርጉ እና ከአቡካዶ ዘይት ለሚጨምቁ፣ ከፍራፍሬም እንዲሁ የተለያየ ነገር ለሚያዘጋጁ፤ ስንዴው ላይ አለ፤ ከዚህ በተጨማሪ ማዕድናትም አሉ። ለእነዚህና ለመሰል ኢንቨስትመንት መሬት አዘጋጅተናል። ለዚህ ያዘጋጀነው መሬት ከ200 ሔክታር መሬት በላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከከተማዋ ጋር በቅንጅት እየሰራ ያለው ስራ ይኖር ይሆን?**

**አቶ ነጂብ፡-** ጅማ ዩኒቨርሲቲ ትልቅ ተቋም ነው። በከተማችን የሚሰራውን የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክት ከዲዛይን ጀምሮ እስከ መስከ ምልከታ እና ክትትል ድረስ ያለው ከእኛ ጋር ነው። ሌላው ከከተማ ግብርና ጋር ተያይዞ ጥናት ከማድረግ እስከ ቦታ መረጣ ድረስ አብረውን እየሰሩ ነው። ለከብት እና ለዶሮ ርባታ ቦታው መሆን ያለበት የቱ ነው? ከሚለው ጀምሮ የቤቱ ግንባታ ድረስ ምን አይነት መሆን አለበት? የሚለውን ጭምር በጉዳዩ ገብተው ጥናት ያደርጉልናል።

ሌላው ቀርቶ እንስሳቱ የሚገዙበት ድረስ በመሄድና ስለጉዳዩ በማጥናት እንዲሁም አይነቱን በመለየት ተገቢውን መረጃ በመስጠት አብረውን እየሰሩ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ስልጠና ይሰጣሉ፤ ድጋፍም ያደርጋሉ። የተሰሩ ፕሮጀክቶችን ከማማከር ጀምሮ አፈጻጸሙንም በመከታተልና ክፍተቶችን ለይተው በመጠቆም አብረውን አሉ። በጥቅሉ በሁሉም አቅጣጫ በከተማው ልማት ውስጥ ተሳትፎ እያደረጉ ነው። እንዲህ ስል ክፍተቶች የሉም ማለት አይደለም። ያለው ስራ በዚህ ደረጃ የሚገለጽ ከሆነ ክፍተቶች ሲፈጠሩም እየሄድን ያለነው በጋራ እያየንና እየፈታን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከጥቂት ሳምንታት በፊት ኢትዮጵያ ከራስ ገዟ ሱማሊላንድ ጋር በባህር በር ዙሪያ ስምምነት መፈጸሟ ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ የተለያዩ አገራት በተቃራኒ የሚመስል መግለጫዎች ሲያስደምጡ ቆይቷል። ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያኑም በጉዳዩ ዙሪያ ተቃራኒ ሐሳብ ሲሰነዝሩ ቆይተዋል። እንደ አንድ የከተማ ከንቲባ ይህንን ሁኔታ እንዴት ይረዱታል?**

**አቶ ነጂብ፡-** ኢትዮጵያ የባህር በር በማግኘቷ እንደ አንድ የጅማ ከተማ እና የኢትዮጵያ ዜጋ የተሰማኝ ትልቅ ደስታ ነው። የባህር በር ማግኘት የሚያስችለን ስምምነት መደረጉ የተበሰረ ዕለት የከተማችን ሕዝብ እና ወጣቱ ወጥቶ ደስታው ሲገልጽ ነበር። ስለዚህም ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት የሚያስችላትን ስምምነት ማድረጓ ትልቅ ደስታ ፈጥሮብኛል።

ከዚህ በኋላም ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ መጠናከር የሚያስችላት ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይ ለወጣቱ ሰፊ የስራ እድል መፍጠር የሚያስችል ይሆናል። ስምምነቱ ከኢኮኖሚ መጠናከር አልፎ ከኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ጭምር የሚያያዝ ነው ብዬ አስባለሁ። ስለዚህ አገሬ ይህንን እድል በማግኘቷ እንደ አንድ ዜጋም ይሁን አመራር ትልቅ ተስፋ እና ደስታ ይሰማኛል። ከዚህም የተነሳ በራሴ በኩል ማድረግ የተገባኝ ነገር ሁሉ ለመፈጸም ፈቃደኛ ነኝ።

ሌሎች ኢትዮጵያ ያገኘችውን የባህር በር እድል ለማጣጣል የሚሞክሩ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የተዳፈሩ ያህል የሚቆጠሩ ናቸው። እንዲሁም ጉዳዩ ተቀባይነት እንደሌለው አድርገው ለመሳል የሚጥሩ የኢትዮጵያ ሕዝብን የናቁ እንደሆኑ ማወቅ መቻል አለባቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የተከበረ ሕዝብ እንደመሆኑ ሕዝብን ማክበር መቻል አለባቸውም። ይህ የባህር በር ስምምነት የአንድ ቡድን ወይም የአንድ ፓርቲ ጉዳይ ሳይሆን የአገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ነው። ስለሆነም በዚህ ደረጃ ተረድተው በተለይ በተቃራኒው የቆሙ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ክብር ቢጠብቁ መልካም ነው ለማለት እወዳለሁ። የፖለቲካ ልዩነት ሁሉ እንዳለ ሆኖ የአገር ጉዳይ ላይ ወደአንድ በመምጣት አንድ አቋም መያዝ ይኖርብናል የሚል አተያይ አለኝ። ስለሆነም እኔ በበኩሌ ከሚቃወሙት ጋር ለመፋለምም ሆነ ስምምነቱን ከሚደግፉት ጎን ቆሜ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ ለመክፈል ፈቃደኛ እንደሆንኩ መግለጽ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ነጂብ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን የኢንቨስትመንት ዘርፉን የማሳደግ ጥረት

**አንተነህ ቸሬ**

የሲዳማ ክልል በሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት የሚያስችል እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ነው። ክልሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚ ዋልታ የሆኑ ምርቶች መገኛ ነው። በርካታ የክልሉ አካባቢዎች በቡና አብቃይነታቸው ይታወቃሉ። ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶችም ይመረቱበታል።

ክልሉ ያለው የተፈጥሮ ሀብት ከግብርናው በተጨማሪ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች እድል የሚፈጥር ነው። በክልሉ ከ17 በላይ የማዕድን ዓይነቶች፣ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስዕቦች ያሉ መሆናቸውም ክልሉን በማዕድን እና በሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንቶች ተመራጭ ያደርጉታል።

ክልሉ የእምቅ ሀብት ባለቤት ከመሆኑ በተጨማሪ፤ በርካታ ስራ ፈላጊ ወጣት የሰው ኃይል መኖሩ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ናይሮቢ የሚዘልቀው መንገድ የክልሉን ዋና ከተማ ሐዋሳን አቋርጦ ማለፉ እና ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መኖሩ በኢንቨስተሮች ተመራጭ እንዲሆን የሚያስችሉት መልካም አጋጣሚዎች ናቸው።

የሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የይርጋዓለም አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክና የመሳሰሉት ትላልቅ የኢንቨስትመንት ተቋማት ያሉት እንደመሆኑም ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚውሉ ምርቶች የሚመረቱበት፣ ለኢንዱስትሪ ተቋማቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለሚያቀርቡ አርሶ አደሮች አቅራቢዎችም ምቹ ገበያ ያለበት ነው።

የክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በ2016 የበጀት ዓመት በክልሉ ለ12 የግብርና፣ ለ34 የኢንዱስትሪ፣ ለ20 የአገልግሎት እና ለ44 የኮንስትራክሽን ዘርፍ ፕሮጀክቶች፣ በአጠቃላይ ለ110 ባለሃብቶች፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዷል። እነዚህ ፕሮጀክቶች ያስመዘግቡታል ተብሎ የሚጠበቀው የካፒታል መጠን ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ነው።

በክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን፣ ፈቃድና መረጃ ዳይሬክተር አቶ ታሪኩ ሮባ እንደሚገልፁት፣ በስድስት ወራት ውስጥ አምስት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ 36 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል። ፈቃድ የወሰዱት ባለሃብቶች በግብርና፣ በማምረቻ፣ በግንባታና በአገልግሎት ዘርፎች የሚሰማሩ ሲሆን፣ ለሁለት ሺ 265 ዜጎች ቋሚ ስራ እድሎችን ፈጥረዋል። ፈቃድ ከተሰጣቸው ፕሮጀክቶች መካከል በሴራሚክ ምርት ዘርፍ ለመሰማራት ፈቃድ የወሰደ አንድ ኩባንያ ይገኝበታል፤ የኩባንያው አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገበ ነው።

አቶ ታሪኩ እንደሚናገሩት፣ በበጀት ዓመቱ ለግብርና ፕሮጀክቶች ፈቃድ መስጠት የተጀመረው በሁለተኛው ሩብ ዓመት ነው። "በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለግብርና ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ አልተሰጠም። አዲስ ፈቃድ ከመስጠት በፊት የቀድሞዎቹን የአፈፃፀም ደረጃ መገምገም አስፈላጊ በመሆኑ በዘርፉ ፈቃድ የወሰዱ ፕሮጀክቶች ኦዲት ተደርገዋል። በግብርና ዘርፍ በገቡት ውል መሰረት ስራ ያልጀመሩና አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ፕሮጀክቶችን የመለየት ስራ ተሰርቷል" ይላሉ።

በሲዳማ ክልል በኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ የሚሳተፉ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን አቶ ታሪኩ ይናገራሉ። ባለፈው የበጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱ ባለሃብቶች (99) መካከል አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች መሆናቸውን አስታውሰው፣ በዘንድሮው የበጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥም በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ለመሰማራት ጥያቄ አቅርበው ፈቃድ ከተሰጣቸው አልሚዎች መካከል አብዛኛዎቹ የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እንደሆኑ ይገልፃሉ።

የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል፣ የኦንላይን (Online) እና የአንድ መስኮት አገልግሎት አሰራሮች ተግባራዊ ተደርገዋል። እነዚህ አሰራሮች ባለሃብቶች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙና ፈጥነው ወደ ስራ እንዲገቡ የተሻለ እድል ፈጥረዋል። ይህም በአጠቃላይ የክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ አፈፃፀም ላይ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።

ዳይሬክተሩ እንደሚያስረዱት፣ የክልሉን ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ሀብት በጥናት መለየት፣ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን የሚጨምሩ ጠንካራና ተከታታይ የፕሮሞሽን ስራዎችን መስራት እና ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ በበጀት ዓመቱ በላቀ ትኩረት እየተከናወኑ የሚገኙ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

አቶ ታሪኩ በክልሉ ሦስት የኢንቨስትመንት የትኩረት አቅጣጫዎች እንዳሉም ጠቅሰዋል። እነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎች የኢንቨስትመንት አቅም ጥናትና የመሬት ዝግጅት፣ ፕሮሞሽን እና ፈቃድና ክትትል መሆናቸውን አንስተው፣ በኢንቨስትመንት ዘርፎች ረገድ ከማምረቻ ዘርፍ በተጨማሪ ክልሉ በአገልግሎት ዘርፍም በሐዋሳ ሀይቅ ዙሪያ ትልልቅ ሆቴሎችንና ሪዞርቶችን በመገንባት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

በግብርናው ዘርፍ ደግሞ፣ አብዛኞቹ የክልሉ አካባቢዎች አትክልትና ፍራፍሬ አብቃዮች በመሆናቸው በእነዚህ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶችም ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ለክልሉ ኢንቨስትመንት፣ በተለይም ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች፣ እድገት ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ እድሎችና ግብዓቶች መካከል አንዱ ከሐዋሳ ከተማ በ45 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ እንደሆነ አቶ ታሪኩ ያስረዳሉ። በአሁኑ ወቅት ከ25 በላይ አልሚዎች ከኮርፖሬሽኑ ጋር ውል ፈፅመው በተለያየ የትግበራ/ስራ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ኩባንያዎቹ በመደበኛ ምርት፣ በሙከራ ምርት እንዲሁም በማሽን ተከላ ላይ ይገኛሉ። ኩባንያዎቹ በአቮካዶ፣ በማንጎ፣ በእንጆሪ፣ በቡና፣ በማር፣ በወተት፣ በስጋ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በአኩሪ አተርና በሌሎች ምርቶች ማቀነባበር ተግባራት ላይ የተሰማሩ ናቸው። በሙሉ አቅማቸው እየሰሩ ከሚገኙት ኩባንያዎች፤ የአቮካዶ ዘይት በማቀነባበር ለውጭ ገበያ፣ ወተት እና የተለያዩ የፍራፍሬ ጭማቂዎችን በማቀነባበር ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲሁም የማር ምርትን ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡት አምራቾች ይጠቀሳሉ። ምርቶቹን ለሀገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ በተጨማሪ ወደ ውጭ ለመላክ በተደረገ ጥረት አበረታች ውጤት ተገኝቷል።

የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ለምርት የሚያገለግለውን የጥሬ እቃ አቅርቦቱን የሚያገኘው ከአካባቢው ማኅበረሰብ ነው። የአካባቢው አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል። አርሶ አደሮቹ የፓርኩ መጋቢ በሆኑ ሦስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት (በንሳ ዳዬ፣ አለታ ወንዶ እና ሞሮቾ አካባቢዎች የሚገኙ) እና በኅብረት ስራ ማኅበራት በኩል የአቮካዶ፣ የማር፣ የወተት፣ የቡናና ሌሎች የግብርና ምርቶችን በፓርኩ ውስጥ ለተሰማሩ ለአልሚዎች እያቀረቡ ነው።

የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የማር እንዲሁም የወተት ምርት የሚያቀርቡ ማኅበራት ግብዓቶችን የሚሰበስቡት በገጠር የሽግግር ማዕከላቱ በኩል ነው። ፓርኩ ግብዓቶችን በማቅረብ የገበያ ትስስርና የገቢ ምንጭ ከተፈጠረላቸው አርሶ አደሮች በተጨማሪ በየዓመቱ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል። ይህ ተግባር የሥራ እድል የመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ ወጪን የማስቀረትና ገቢ ምርትን የመተካት ድርብርብ ዓላማዎች አሉት።

ከሦስት ዓመታት በፊት ትልቅ ገበያ ያልነበረው የአቮካዶ ምርት በአሁኑ ወቅት ደረጃ ወጥቶለት አርሶ አደሩ በስፋት ምርቱን እያቀረበ፣ ገቢ እያገኘና አዳዲስ ዝርያዎችን እያለማ ነው። ፓርኩ አርሶ አደሩ ጥሬ እቃን በብዛትና በጥራት እንዲያቀርብ እድል እየፈጠረ ነው። ይህም የግብርና ምርታማነት እንዲጨምርና የአርሶ አደሩ ሕይወት እንዲሻሻል እያደረገ ነው።

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ካሏቸው ፋይዳዎች መካከል አንዱ ፕሮጀክቶቹ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረጋቸው ነው። በዚህ ረገድ በሲዳማ ክልል የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአካባቢውን ሕብረተሰብ በተለያዩ መንገዶች ተጠቃሚ እያደረጉ እንደሚገኙ አቶ ታሪኩ ይገልፃሉ።

ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ሲሰማሩ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ ከሚያደርጉባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ የሥራ እድል ፈጠራ ነው። የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቹ ለበርካታ የክልሉ ነዋሪዎች የስራ እድል ፈጥረዋል። ከስራ እድል በተጨማሪ የክልሉ ሕዝብ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በገበያ እድልም ተጠቃሚ ሆኗል።

እንደ አቶ ታሪኩ ገለፃ፣ በ2016 ዓ.ም የበጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ 207 አርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። አርሶ አደሮቹ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ ከሆኑባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ግብርና ነው። በግብርና ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለአርሶ አደሮች ዘመናዊ የምርት ዘዴዎችንና ግብዓቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርገዋል። ለአብነት ያህል በዶሮ እርባታ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች አርሶ አደሮች ዘመናዊ የዶሮ እርባታ ስልት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻላቸው እንዲሁም በንብ እርባታ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሀብቶች ዘመናዊ ቀፎዎችን ለአርሶ አደሮች በነፃ ማቅረባቸውና ስለአጠቃቀሙም ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረጋቸው የዚህ ተሳትፎ ማሳያ ተደርገው የሚጠቀሱ ናቸው።

ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ስራዎቻቸውን በሚሰሩባቸው አካባቢዎች የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ተግባራትን ስለሚያከናውኑ በዚህ ተግባር በኩል በርካታ የክልሉ ሕዝብ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆኗል። በክልሉ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን በመገንባትና የትምህርት ግብዓቶችን በማቅረብ ለአገልግሎት አብቅተዋል።

የመንገድ መሰረተ ልማት በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ አለመሆን፣ የብድር አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለመመቻቸት እንዲሁም በመስመር ዝርጋታ እና በትራንስፎርመር እጥረት ምክንያት የሚፈጠር የኃይል አቅርቦት እጥረት በክልሉ የኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ የተጋረጡ መሰናክሎች እንደሆኑ አቶ ታሪኩ ይናገራሉ። ለኢንቨስትመንት የተዘጋጀ መሬት ወደ መሬት ባንክ ገቢ ያለመሆን፣ ባለሀብቶች በገቡት ውል መሰረት ያለማልማት፣ የሚሰጡ አገልግሎቶች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ያለመደገፍ ችግር እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ክፍተቶች በበጀት ዓመቱ እቅድ አፈፃፀም ላይ ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው ከተለዩት ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ።

አቶ ታሪኩ "ከዘርፉ መሰናክሎች መካከል አንዱ የኃይል አቅርቦት ችግር (የኃይል አቅም ማነስና መቆራረጥ) ነው። የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው ወደ ስራ የገቡ ባለሀብቶችም ቅሬታ የሚያቀርቡበት የመሰረተ ልማት ዘርፍ ነው። በተለይ በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የኃይል አቅርቦት እንዲስተካከልላቸው በተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ። በፋይናንስ አቅርቦት ረገድም የኢንቨስትመንት ፕሮፖዛሎችን ገምግሞ ፈጣን ምላሽ ያለመስጠት ችግር ይስተዋላል። ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ችግሮቹን ለማቃለል ጥረት እያደረግን ነው። ችግሮቹን ሙሉ በሙሉ መፍታት ባይቻልም እንዲቃለሉ ተደርጓል" ይላሉ።

> **የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል፣ የኦንላይን (Online) እና የአንድ መስኮት አገልግሎት አሰራሮች ተግባራዊ ተደርገዋል። እነዚህ አሰራሮች ባለሃብቶች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙና ፈጥነው ወደ ስራ እንዲገቡ የተሻለ እድል ፈጥረዋል። ይህም በአጠቃላይ የክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ አፈፃፀም ላይ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል**

# ጎሜ

## ከምስጋና ይልቅ ለነቀፌታ የሰሉ አንደበቶች

**አሲ ሴሮ**

በሰለጠኑት አለማት ከሚታዩ የሚያስቀኑ ባህሎች መካከል መመስጋገን አንዱና ዋነኛው ነው። በእነዚህ ሀገራት በትንሽ በትልቁ መመስጋገንና መበረታታት በስፋት ይታያል። ከህጻን እስከ አዋቂው፤ ከሴት እስከ ወንዱ፤ ከተማረው እስካልተማረው ድረስ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር የምስጋና አጠቃቀማቸው ነው። ይህ ደግሞ የእድገታቸውም አንዱ ምክንያት እንደሆነ ይሰማኛል።

በድንገት በእነዚህ የሰለጠኑ ሀገራት የተገኘ ኢትዮጵያዊ አንዱ ከሚያስገርሙትና ምናልባትም ከሚያስቀኑት ተግባራት መካከል በየአጋጣሚው የሚሰሙ የምስጋና ቃላት ናቸው። እዚህ ኢትዮጵያ እንደዳይኖሰር ሊጠፉ ከተቃረቡት ቃላት ውስጥ አንዱ የሆነው ‹‹አመሰግናለሁ›› የሚለው ቃል በውጭው ዓለም በብዛት ጥቅም ላይ ከሚውሉት አንዱ ነው። በየትራንስፖርቱ፤ በየሆቴሉ፤ በየመዝናኛ ስፍራው፤ በየመንገዱ ‹‹አመሰግናለሁ›› መባባል የተለመደ ነው።

ኢትዮጵያውያን ጀግኖችና ጨዋዎች ብንሆንም የምስጋና ድሃዎች ነን። በጣም በሳሳ መልኩ ከምንጠቀምባቸውና በሂደትም እንዳይጠፉ ከምፈራላቸው ቃላት መካከል ምስጋና አንዱ ነው። ‹‹አመሰግናለሁ›› የሚለውን ቃል በእጅጉ የምንፈራው ይመስለኛል። ከዚያ ይልቅ መውቀስ፤ መርገም፤ ማጣጣልና ማንቋቋሽሽ ይቀናል። በተለይ በአሁኑ ወቅት ሁሉም ስራዬ ብሎ የተያዘው እና እንደ ዕውቀትም እየተወሰደ ያለው ከማመስገን ይልቅ መውቀስና መተቸት ይመስለኛል። እነዚህ አሉታዊ ቃላት ምስጋናና ደፍጥጠው መድረኩን የተቆጣጠሩት ይመስለኛል።

ሆኖም ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ምስጋና ነው። ምስጋና የመከባበርና መተባበር መገለጫ ነው። ይህም አንድነትን የሚያጠናክር ትልቅ ኃይልም ነው። ተስፋችን ብዙ መሆኑን በመረዳት ነገን በአዎንታዊ ኃይል የምንገነባው ዛሬ ላይ እርስ በእርሳችን ስንመሰጋገንና አርአያዎቻችንን ማመስገን ስንችል ነው። ኢትዮጵያ የገጠሟትን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ተቋቁማ በአሸናፊነት ያለፈች ሀገር መሆኗን በመናገር፤ ከሆነባት ይልቅ የሆነላት ይበልጣልና ፈጣሪንም ጀግኖች ልጆቿንም ማክበርና ማመስገን የግድ የሚል ነው።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ፈጣሪን ከመፍራት፣ ከማክበር እና ከማመስገን ወደኋላ ያለችበት ጊዜ የለም። ይህ በመሆኑ ኢትዮጵያ ስታሸንፍ ቆይታለች። በአድዋ ጦርነትም ሆነ ሌሎች ኢትዮጵያ በተሳተፈችባቸው ጦርነቶች ጀግኖች እርስ በእርሳቸው በመመሰጋገናቸውና በመከባበራቸው ይሸነፋሉ የማይባሉ የኢትዮጵያ ጠላቶችን ማሸነፍ ተችሏል።

በተለይም የሀገር ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ ልዩነትን አቻችሎና ለሌላ ጊዜ አሸጋግሮ ለሀገርና ለወገን የተሰጠን ክብር አብሮ ማጣጣም ያስፈልጋል። ሀገር ስትሸለም የሚሸለመው መሪዋ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋ ነው። የሀገር ስኬትም ሆነ ውድቀት የጋራ መገለጫዎቻችን ስለሆኑ ለጠላቶች አሳልፎ በሚሰጥ መልኩ የሚሰጡ ሽልማቶችንና ዕውቅናዎችን ማጣጣልና ማሳነስ ከአንድ ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም።

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝም ሰሞኑን ኢትዮጵያና መሪዋ በውጭው ዓለም በስፋት ሲመሰገኑ እኛ ለጉዳዩ ሩቅ ሆነን ከመገኘታችንም በላይ አንዳንዶቻችን ለትችት የቀደመን አለመኖሩ ነው። በተለይ አንቂዎችና ፖለቲከኞች ነን ባዮች ቀድመን ማመስገን ቢያቅተን እንኳን በውጭው ዓለም ለሀገርና ለመሪ የተሰጠውን ምስጋና ለመተቸት መሯሯጣችን ምን ያህል ከምስጋና ጋር እየተራራቅን እንደመጣን ማሳያ ነው።

> **ሀገር ስትሸለም የሚሸለመው መሪዋ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋ ነው። የሀገር ስኬትም ሆነ ውድቀት የጋራ መገለጫዎቻችን ስለሆኑ ለጠላቶች አሳልፎ በሚሰጥ መልኩ የሚሰጡ ሽልማቶችንና ዕውቅናዎችን ማጣጣልና ማሳነስ ከአንድ ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም**

የተባበሩት መንግስታት የምግብ እና የእርሻ ድርጅት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ላበረከቱት አስተዋጽኦ እና አመራር በሚል ለጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የከበረውን የፋኦ አግሪኮላ ሜዳልያ ሸልሟል።

እንደ መንግስታቱ ድርጅት መረጃ ከሆነ ሽልማቱ የሚሰጠው የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ልዩ አበርክቶ ላበረከቱ ታዋቂ እና የተከበረ ስብዕና ላላቸው ሰዎች ነው።

ሽልማቱ በጣሊያን ሮም ከተቀበሉ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ሽልማቱን ያበረከተላቸውን የመንግስታቱ ድርጅትን በማመስገን "ከፍ ያለ ጠቀሜታ ባላቸው እና የኢንዱስትሪ ግብዓት በሆኑ የግብርና ምርቶች ላይ ትኩረት መደረጉ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እያስገኘ" እንደሚገኝም ገልጸዋል፤ "የምግብ ሉዓላዊነት ጉዟችንን በፅናት እናስቀጥላለን" ብለዋል።

ጠ/ሚኒስትሩ ይገባቸዋል ከሚል አስተያየት ጀምሮ ሽልማቱ በጠ/ሚኒስትሩ ደጋፊዎች ዘንድ ውዳሴ ተችሮታል። የጠ/ሚኒስትሩ የውጭ ጉዳዮች አማካሪ የሆኑት እና በመንግስታቱ ድርጅት የቀድሞ የኢትዮጵያ አምባሳደር ታዬ አስቀስላሴ የዓለም የምግብ እና እርሻ ድርጅት ለጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ሽልማት ማበርከቱን አወድሰው "እርግጥ ነው የገበሬዎች ህይወት ሲሻሻል የሀገሪቱም እንዲሁ ይሻሻላል" የሚል አስተያየት በኤክስ የማህበራዊ ትስስር ገጻቸው አስፍረዋል። ከዚሁ ምስጋና ጊን ለጎን ደግሞ ትችት ብቻ አንደበታቸው የለመዱ ሰዎች ነቀፌታ አዘል አስተያየት ሲሰነዝሩ ይደመጣሉ። ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፋኦ ሽልማት ያገኙት ባለፉት ዓመታት በጠንካራ አመራራቸው በተለይ በግብርናው ዘርፍ ባስመዘገቡት ውጤት ነው።

ኢትዮጵያ በግጭቶች፣ መከራዎችና ረሃብ ስትፈተን የቆየች ሀገር ብትሆንም አሁን ላይ ግን ካለፈው ትምህርት ወስዳ ሁኔታዎቹን ወደ ዕድል እየቀየረች ያለች ሀገር ነች። ቀደም ሲል በጦርነት፤ በርሃብና ድርቅ የሚታወቀውን ስሟን የሚለውጡ ስራዎችንም በማከናወን ላይ ትገኛለች።

በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በግብርና፤ በአረንጓዴ አሻራ፤ በኃይል አቅርቦት እና በቱሪዝም ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት የሀገሪቱ መጻኢ ዕድል ተስፋ ሰጪ እንደሆነ የሚያመላክቱ ናቸው። ባለፉት አምስት ዓመታት በተደረጉ ጥረቶች በምግብ ሰብል እራሷን ከመቻል አልፎ ስንዴን እና አቦካዶን የመሳሰሉ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ አዲስ ታሪክ በመጻፍ ላይ ትገኛለች።

ግብርና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና 120 ሚሊዮን የሚጠጋውን ሕዝብ የሚመግብ ዘርፍ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ 96 ሚሊዮን ወይም 80 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ኑሮው ቀጥታ ከግብርና ስራ ጋር የተያያዘ ነው። ከውጭ ምንዛሬ አንጻርም ብንመለከተው አብዛኛው ድርሻ የሚገኘው ከዚሁ ዘርፍ ነው።

ይህንኑ ሃቅ በመገንዘብ በተለይ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት አበረታች ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል። የሀገሪቱን መልክዓምድርና የአየር ጸባይን መሰረት ያደረጉ ስራዎች በመሰራታቸው ጤፍን የመሳሰሉ ምርቶች ምርታማነት ከመጨመሩም ባሻገር ኢትዮጵያ በታሪኳ አምርታቸው የማታቃቸው የበጋ ስንዴና ሩዝን የመሳሰሉ ሰብሎች ከራስ ፍጆታ አልፈው ለውጭ ገበያም ለመቅረብ ችለዋል።

ጤፍ በርካታ ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ የሚመገበው እና አብዛኛውን የእርሻ መሬት የሚሸፍን ቢሆንም ለበርካታ ዓመታት ይሄ ነው የሚባል የምርት ዕድገት ሳያሳይ ቆይቷል። የለውጡ መንግስት እውን እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ በአጠቃላይ የነበረው ዓመታዊ ምርት ከ300ሚሊዮን ኩንታል ብዙም የዘለለ አልነበረም። ባለፉት አምስት ዓመታት ጤፍን በክላስተር ማረስ በመቻሉ ምርቱ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ዓመታዊ ምርቱ 639 ሚሊዮን ኩንታል ሊደርስ ችሏል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በአዲስ የልማት ጎዳና እንድትራመድ ካደረጓት የግብርና እንቅስቃሴ አንዱ የስንዴ ልማት ነው። ቀደም ሲል በጥቂት መጠን፤ በተወሰኑ አካባቢዎች፤ በክረምት ብቻ ይመረት የነበረውን የስንዴ ልማት ወደ በጋም በማሸጋገር የስንዴ ምርትን ከራስ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያም የማቅረብ አቅም ላይ ተደርሷል።

የስንዴ ምርት በ2014/15 ዓ.ም የምርት ዘመን ወደ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በሄክታር ሁለት ቶን ይገኝ የነበረው የስንዴ ምርትም ወደ አራት ቶን ማሳደግ ተችሏል።

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በ2016 ምርት ዘመን ወደ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 117 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማምረት እየተሠራ ነው። አሁን ላይ ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት ቀዳሚ ስንዴ አምራች ለመሆን በቅታለች። በ2015 ዓመት ብቻ 32 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ መቅረቡ የዚሁ ስኬት አንዱ ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ እንደ ስንዴው ሁሉ ለሩዝ ምርት ትኩረት በመስጠት ከሀገራዊ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ለመላክ በትኩረት በመስራት ላይ ትገኛለች። በተለይም ሀገሪቱ ለሩዝ ምርት ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይና ምቹ መሬት ያላት መሆኑ ያቀደችውን ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደማያዳግታት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለከተውም በኢትዮጵያ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር በሩዝ መልማት የሚችል መሬት ቢኖርም በየዓመቱ ከ200 ሺህ ቶን በላይ ሩዝ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ 200 ሚሊዮን ዶላር ወጭ ታደርጋለች።

ሆኖም በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ስርዓት መተግበር ከጀመረ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግስት ፊቱን ወደ ሩዝ ምርት በማዞር በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል። በተለይ በአማራ ፎገራና በጅማ አካባቢ እየተከናወነ ያለው የሩዝ ምርት ኢትዮጵያን ከሩዝ ተቀባይ ሀገርነት ወደ ላኪነት የሚያሸጋግራት ነው።

የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ከ35-40 በመቶ የሚሸፍነው ቡናም ምርታማነቱ ጨምሯል። 500ሺ የነበረው ዓመታዊ ምርትን ወደ 800ሺ ማሳደግ ተችሏል። በዚህም 700ሚሊዮን ዶላር የነበረው የውጭ ገቢ ወደ 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ ችሏል። የሻይና ቅመማ ቅመም ዘርፍን ምርታማነት ማሳደግ በመቻሉ ለሀገሪቱ እስከ 20 ሚሊዮን ዶላር የማምጣት አቅም ላይ ደርሷል።

ከዚህ ባሻገርም በሌማት ትሩፋት ንቅናቄ በሁሉም ክልሎች ከፍተኛ ምርታማነት ታይቷል። በማር፤ በእንስሳትና በእንስሳት ተዋጽዖ፣ በጓሮ አትክልትና በፍራፍሬ ምርት ላይ የጎላ ለውጥ መጥቷል። በዚህም ዜጎች እየተፈጠረ ያለውን የዋጋ ግሸበት እንዲቋቋሙ፣ ተጨማሪ የሥራ ዕድል እንዲያገኙና ብሎም ከራሳቸው ተርፎ ለገበያ እንዲያቀርቡ አስችሏል።

በአጠቃላይ በግብርናው ዘርፍ ያለው መሻሻል ስንዴን፤ ሩዝንና አቦካዶን የመሳሰሉ ምርቶችን ከሀገር ውስጥ አልፎ ለውጭ ገበያም እንዲቀርብ ያደረገ ነው። ይህ ደግሞ በውጭ ታዛቢዎች ጭምር የተመሰከረለትና ኢትዮጵያም በግብርናው ዘርፍ እምርታ እያሳየች መምጣቷን ያሳየ ነው።

# የዘመን ጥበብ

# “ክብር ለጥበብ”

ሙሉጌታ ብርሃኑ

እኔ አይደለሁም፤ አርዕስቱ ነው ያለው። እኔም ‘’አሜን!!” ብያለሁ። ታዲያ አርዕስቱ ማን ነው፤ የማን ነው? ብሎ ለጠየቀ፤ ጥያቄው አግባብ ነውና ልመልስ ግድ ይለኛል። ይህን ያለውም፤ ለዘመናት ሲገፉ ለኖረው የኪነ ጥበብ ባለሙያ፤ “የተሰበረውን ልቡን ለመጠገን እሻለሁ” በማለት ከሦስት ዓመታት በፊት የተነሳው አንድ ለ’ናቱ ነው። እሱም የ”ክብር ለጥበብ” ዓመታዊ የዕውቅናና የሽልማት ሥነ ሥርዓት ነው። አንድ ለናቱ ማለቴ፤ እንደ መንግሥት በአሁኑ ሰዓት ለሀገራችን የኪነ ጥበብ ባለውለታዎች ዕውቅና ለመስጠት ብቸኛው ዓውደ ሽልማት በመሆኑ ነው።

መሸለሙን፤ ያየ የሰማ ሁሉ ይሸልም ይሆናል። ዕውቅና ለመስጠቱ ግን ዕውቅና ያስፈልጋል። መቼም የደረሰና ደስ ያለው ሁሉ እያነሳ ፊት ላይ የሚመርገው ባለመሆኑ ነው። ስለዚህ አንድ ለ’ናቱ ካልኳችሁ ከክብር ለጥበብ ዕውቅና በስተጀርባ አንድ እውቅ አካል አለ ማለት ነው። አዎን፤ እርሱም የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ነው።

ይህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ካሉበት ኃላፊነቶች አንዱ በኪነ ጥበብ ዘርፍ በሚከናወኑ ተግባራት እጅ ከማስገባቱም በዘለለ ትልቅ የሆነ የባለቤትነት ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

የሆነው ሆነና በአሁኑ ሰዓት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የጀመረው የ”ክብር ለጥበብ” ዓመታዊ የዕውቅና ዝግጅት፣ ከባዶ አንድ ይሻላል “እሰየው!” የሚያስብል ነው። ከምንም ደግሞ አንድ ለናቱ ይበጃል። ታዲያ ባሳለፍነው ሳምንት ይህን በተመለከተ ተቋሙ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቶ ነበር። በዛሬው የዘመን ጥበብ አምዳችንም ከዚሁ መግለጫ ላይ እየዘገንን፤ ማወራረጃ ይሆነን ዘንድም ከማይጎድለው የጥበብ ውሀ ምንጭ ጨለፍ እያደረግን መጎንጨታችን እንቀጥላለን።

“ክብር ለሚገባው ክብርን እንሰጣለን!” አሉ፤ ክብርት ሚኒስትር ዴኤታዋ። መግለጫውን በሰጡበት መድረክ ላይ ነበር ይህን ያሉት። ክብርት ወ/ሮ ነፊሳ አልማህዲ በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የኪነ-ጥበብ ስነ-ጥበብና ፈጠራ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ናቸው። ለዛሬው የመነሻ ሀሳብ የሆነንን፣ ሙሉውን ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡትም እኚሁ ሴት ነበሩ። ተቋሙ በ”ክብር ለጥበብ” የሽልማትና ዕውቅና መንገድ መጓዝ ከጀመረ የዘንድሮው ለሦስተኛ ጊዜ ቢሆንም የዘንድሮው ግን ለየት ያለ ስለመሆኑ አስቀድመው ጠቆም አድርገው ነበር። ድግሱም በብዙ ባለሙያዎች የተሰናዳ በመሆኑ፣ የጥበብን ጣት የሚያስቆረጥም እንደሚሆንም የመግለጫው ሽታ ያሳብቃል። ለመሆኑ “ክብር ለጥበብ” ምንድነው? አላማውስ? ነገሩ እንግዳ አይደለም። በዕድሜ፤ የሦስት ዓመት ጨቅላ ቢመስልም፤ ሥራና ግብሩ ግን ገዘፍ ያለ ነው። የዝግጅቱ ዋና ዓላማ በኪነ ጥበብ ዘርፍ የሀገር ባለውለታ ሆነው ያለፉትንም ሆነ የተረሱትን ማስታወስ፤ ያሉትንም “ከጎናችሁ ነን” ብሎ ማበርታት ነው።

በ2013 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ አሀዱ ብሎ ጀመረ። የዚያን ጊዜ ታዲያ የሽልማት እንጂ የዕውቅና አልነበረም። ነገሩም በውድድር ነበረ። በዚህም ምክንያት በክብር ለጥበብ የ2013 ገጽ ላይ ሦስት ጥቋቁር ነጠብጣቦች ነበሩበት ለማለት እንችላለን። የመጀመሪያው ጥቁር ነጥብ፤ የውድድር መሆኑ ነው። ኋላና ፊት፤ ግራና ቀኝ አሻግሮ ከማየት ይልቅ በጊዜያዊ የውድድር መንፈስ የታጠረ አድርጎታል። ሁለተኛ ነጠላ እይታ ነው፤ የሚሸለሙ አካላት የሚመዘኑት በወቅቱ ባሳዩት ጊዜያዊ ሥራና ብቃት በመሆኑ ቀደም ሲል ድንቅ ሥራ ላበረከቱ እድሉን ያጠብባል። በሦስተኛ ደረጃ ሁሉን አካታች ካለመሆኑም በላይ በሕይወት የሌሉትን ከጨዋታ ውጭ ማድረጉ ነው።

2ኛው ዙር በ2014 ቀጠለ። ክብር ለጥበብ ማሊያውን ቀይሮ መጣ። ከውድድር ይልቅ የወዳጅነት መንፈስ ይኖረው ዘንድ የሽልማት ሳይሆን የዕውቅና እንዲሆን ተደረገ። ሌላም አለ፤ በ1ኛው ዙር ያልተካተተው የሙዚቃ ዘዋሪ (የዲጄ) ዘርፍ እንዲካተት ተደረገ። ከለውጡ ስር ጥቁሩ ነጥብ እዚህም ነበር። የፍትሀዊነቱ ነገር ከማጠያየቅም የሚያነጋግር ጉዳይ ሆኖ ታየ። በአንዳንድ ነገሮቹ በቂ ጥናትና ዝግጅት የተደረገበትም አይመስልም ነበር። መድረክ ላይ ወጥቶ የነበረ አንድ ሙዚቀኛ፤ ይገባሃል ተብሎ ሽልማቱን ከተቀበለ በኋላ እዚያው ከመድረኩ ላይ እንዳለ፤ በስህተት ነው በማለት



**በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ስለ ሀገራቸው ደም እንባ ተፍተው፤ ለነብሳቸው እንኳን ሳይሳሱ እንደ ሳንባ በርተው፤ እንደ ሻማ የቀለጡ እጅግ ለቁጥር የሚታክቱትን አረግጠን አልፈናል**

ተቀይሮ በምትኩ ሌላ እንዲሰጠው ተደርጓል።

በዚህ ብቻም ሳይሆን ዕውቅናው የሚገባው ለማን ነው፤ የሚለው በቅጡ ያልተጠናበት መሆኑም በግልጽ የሚታይ ነበር። እንዲህ ቢሆንም ቅሉ፤ ከጥሩነትና ከምስጋና የሚያጎድለው ግን አልነበረም። ቀጣዩ 2015፤ ጥቁርም ነጭም የሌለበትና ምንም ያልተጻፈበት ባዶ ገጽ ነበር። ሳይካሄድ ቀረና፤ ለ2015 ያሏት ሦስት ዞራ ለ2016 ሆነች። 3ኛው ዙርም በትላንትናው የጥር 22 ላይ አረፈ።

2016 በክብር ለጥበብ ውስጥ ያለፉትን ዓመታት ሁሉ ልታስንቅ ወገቧን ታጥቃ ሸብ ረብ እያለች ስለመሆኗ አስቀድሞ ተነግሯል። “ያለፉት ዙሮች ብዙ ተምረንባቸዋል። የታዩብንን ደካማ ጎኖቻችንን ጥለን፤ መቀጠል ባለባቸው ጠንካራ ጎኖቻችን ላይ አዳዲስ ነገሮችን በማከል፤ 2016ን በተለየ አመጣጥ መጥተናል” ላሉት ነፊሳ አልማህዲ፤ እኛም ‘እንኳን በደህና መጣችሁ!’ በማለት፤ ተቋማቸው ይዞ የመጣውን የዘንድሮውን የክብር ለጥበብ ስጦታ በደስታ መቀበል ጨዋነት ነው። ታዲያስ ክብር ለጥበብ በ2016 ምን ይዞ እንዴትስ መጣ? ይዞት እንደሚመጣቸውና ከተነገሩት አንዱና ትልቁ፤ ዕውቅናው የሕይወት ዘመን ከመሆኑም ‘ሥራውን ለሠሪው፤ ሙያውን ለባለሙያው’ የተወ መሆኑ ነው።

ዕውቅና የሚሰጣቸውን ባለውለታዎች የመምረጡን ኃላፊነት ለየዘርፉ አዋቂዎች ሰጥቷል። ይህ የነበረውን የፍትሀዊነት ጥያቄ ለመመለስ ሁነኛው መንገድ ነው። ለዚህም ሲባል ረዥም ጊዜ የፈጀ ዝግጅት በማድረግ በእያንዳንዱ የኪነ ጥበብ ዘርፍ፤ ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ተሸላሚዎቹን የሚመርጡ አቢይ ኮሚቴዎች ተዋቅረው በጥናት ላይ ሰንብተዋል። በአዲስ አበባ ቅጥር ላይ ብቻ ሲሽከረከር የነበረው ይህ ዕውቅና፤ ከበባውን ጥሶ ወደ መላው የሀገሪቱ ክፍል በመስፋት ሀገር አቀፍ ሆኖ መጥቷል። ከወጣት እስከ አንጋፋ ያሉ የጥበብ ባለሙያዎች ለክብር ይታጨቡበታል፤ በዕውቅና ይሞሸሩበታል።

2016 እና ኪነ ጥበብ፤ ዘንድሮና ክብር ለጥበብ፤ 50 ያህል የክብር ኒሻኖች በዕውቅና ሙዳይ ውስጥ ተቀምጠዋል። በዘርፉ ውስጥ የተካተቱ 12 ኪነ ጥበባት ከዚህ ክብር ለመቋደስ ልባቸውን ከፍተው ይጠባበቃሉ። ከእያንዳንዱም እንደ ስፋትና ግዝፈታቸው ከ3 እስከ 5 ያህል ጥበበኞች ይመረጣሉ። በድምሩም እስከ 50 ሰዎች ዕውቅናውን ያገኛሉ። “ይህን ጥሶ የመጣው ማን ይሆን?” የሚለውን ጥያቄ መመለስ የሚችሉትም የኮሚቴው አባላት ብቻ ናቸው።

መነሻችን ወደ ነበረው እለት እንመለስና የክብር ለጥበብ መግለጫ በተሰጠበት ወቅት ጋዜጠኞች ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት፤ ክብርት ነፊሳ አልማህዲ ያነሷቸው ሌሎች ሀሳቦችም ነበሩ። ከእነዚህም አንደኛው በኪነጥበቡ የማይዘነጋ አሻራ ያሳረፉትን ዕውቅና ከመስጠቱ ባሻገር መንግሥት ፊቱን ወደ ኪነ ጥበቡ አዞሮ ዘርፉንና ባለሙያውን በቋሚነት እንዲያግዝ ስለማድረግ ነበር።

“ኪነ ጥበቡና መንግሥት ፊት ለፊት የሚገናኙበት ድልድይ አለመኖሩ ትልቁ ችግር ሆኗል። ስለ ዘርፉ፤ በሕገመንግስቱ የተቀመጠ ምንም ነገር የለም፤ በመሆኑም አዋጅም ሆነ የተለያዩ ደንቦችን ለማርቀቅ እኛም ፈተና ሆኖብናል። ከዚህ አንጻርም መንግሥትን ለመጠየቅ የሚያስችል አግባብ አለመኖሩ ነው። ቢሆንም ተስፋ ሳንቆርጥ ነገሮችን ለመቀየር በመሥራት ላይ ነን” ሲሉ ነበር የተናገሩት። “እየሠራንበት ነው” ካሏቸው ጉዳዮችም አንዱ፤ የዘርፉ ባለሙያዎች ስለሚገለገሉባቸውና በውድ ዋጋ ከውጭ ስለሚገቡት ቁሳቁሶች ሲሆን፤ የተጫነባቸው ከባድ የሆነ የቀረጥ ቀንበር እንዲነሳላቸው ከሚመለከተው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር ላይ ስለመሆናቸው ገልጸውታል። በኪነ ጥበቡና በመንግሥት መሀከል ትልቅ ግንብ ስለሆነው ሕጋዊ ጉዳይም እንዲሁ በመፍትሔ ፍለጋ መንገድ ላይ ስለመሆኑ።

“ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም” ቢሉም አበው፤ ክብር ለጥበብን እንደተደገፍን በሀሳብ ጥቂት አሸልበን፤ በሽለብታው ሰመመን አንዳንድ ነገሮችን እንይ።

ደጋግመን ስለጉድለቶቻችን ማንሳታችን፤ ለነቀፌታ ሳይሆን እንዲያው የተሻለ ሆኖ ለማየት ካለን ጉጉትና ከዚህ በላይ እዚህ ጋር መቆየት እንደሌለብን በአንክሮ ለማሳሰብ ነው። ካነሳን አይቀርም በሽለብታው ይቺን ለመጠየቅ ወደድኩ፤ የኛ ኪነ ጥበብ ወላጅ አልባ፤ ባለቤት አልባ መስሎ እድሜ ዘመኑን ጉስቁልቁል ማለቱ ለምንድነው? ስል እራሴን ጠይቄ ምላሹንም ከራሴው ጠበቅኩኝ፤ እናም እኚህኑ ምላሾች አገኘሁ። ስለሌለን ሳይሆን ስላልገባን ነው። ባለቤት ሆነን የኔ ነው ማለቱን እንፈራለን።

ግራ ቀኙን ቢመለከት አጥብቆ የሚይዘው አለመኖሩን ስለተረዳም ይሁን ብቻ፤ ኪነ ጥበቡም በሞቀበት ሁሉ እየዞረ ሲሟሟቅ ከርሟል። ወላጅ አልባነት፤ ባለቤት አልባነትም የተሰማው እንደሆነም አንዳንዴ ቁዝም ይላል። ሌላው ቀርቶ፤ እንደ ሀገር ያሉትን የሽልማት ተቋማት ብንመለከት እንኳ በኪነ ጥበቡ ምን አይነቱ ድርቅ ገባ የሚያስብል ነው።

በአብዛኛዎቹ ሀገራት የሚሠራ ሰው ይኑር እንጂ በሰበብ አስባቡ እስኪመስል ድረስ ሽልማቱ በሽበሽ ነው። እንደኛ፣ ወደ መንግሥት ዞረን ብንጠይቅ ... ነጥብ ላለመጣል ታህል አንድ ለናቱ የ”ክብር ለጥበብ” አለ። ከዚህ ወጣ ስንል ደግሞ፤ በዋናነት ሁለት ተቋማት ተጠቃሽ ናቸው፤ “ለዛ” እና “ጉማ” አዋርድ የተሰኙት የሽልማት ተቋማት። ካላቸው ጥሩ ነገሮች ጎን የሚነሳባቸው ጥያቄ ቢኖርም ልንጠቅስም ሆነ በቋሚነት “አሉን” ልንል የምንችለውም እነዚህኑ ነው።

በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ስለ ሀገራቸው ደም እንባ ተፍተው፤ ለነብሳቸው እንኳን ሳይሳሱ እንደ ላንባ በርተው፤ እንደ ሻማ የቀለጡ እጅግ ለቁጥር የሚታክቱትን እረግጠን አልፈናል። ውለታን የምንበላ ውለታ ቢስ ሆነንም አይደለም። ደግሞም ለመስጠት የምንፈራ ንፉጎችም አይደለንም። አብዛኛውን ጊዜ አንዳንዶች ወድቀው የተረሱ መሆናቸውን አይናችን እያየ፤ ልባችንም እያወቀ፤ ታዲያ ለምንድነው ከንፈር መጦ ዝምታን የምንመርጠው? ምክንያቱም፤ “አመሰግናለሁ!” ከማለት ይልቅ “ሙያ በልብ ነው” ብለን፤ ክፉውንም ደጉንም ዋጥ ማድረጉን እንወዳለን።

ብዙውን ጊዜ ደግሞ፤ ባለቤቶቹ እኛው እራሳችን መሆናችንን ስለማናምንበት ከኃላፊነቱ እራሳችንን እናገላለን። ለዚህ፤ ከኛ ውጭ የሚመጣና ማድረግ ያለበት ሌላ አካል አለ ብለን ስለምናስብም፤ አንዱ ለአንዱ እየተዋቸው ባለውለታዎቻችን በመሀል ቤት ተረስተው ይቀራሉ። ጥበበኛ ልጆቿ ሲሙቱ የምትደማው ጥበብ ናት። የወደቀውን ልጇን አይዞህ! ብለን ስናነሳው፤ የምናነሳው እራሷኑ ጥበብን ነው። ቀላል ነገር አይደለም ለብዙ ዘመናት ሲጎትተን የኖረው ነገር፤ ለኪነ ጥበብ የሚያዝን ጥሩ ልብ ስለጠፋ ሳይሆን እነዚህን ልበ ደጋጎች፤ ለአንድ ዓላማ የሚሰበስብ መጥፋቱ ነው።

ኪነ ጥበቡ የትልቅ ትንሽ ሆኖ የታየው በግለሰብና ባለሀብቱ ዘንድ ብቻም ሳይሆን በመንግሥትም ጭምር ነው። ሕገ መንግሥቱ እንኳን ይህን ያህሉን ፍሪዳ በሬ፤ እንደ እንቦሳ ጥጃ ከበጎቹ ጋር አስሮት ቆይቷል። የሚሰጠውም መኖ የበጎቹን ያህል ነውና ሳይበላ ቢከርም ጊዜ፤ ዛሬ ላይ ቆርቁዞ ከሰባው ይልቅ ከሲታውን አስመለከተን። ይሄው ዛሬም ድረስ “አንተ የጥበብ እንቦሳ፤ ምነው የማታድግ? ማንስ ነው የረገመህ?” እንዳልን አለን። የሚረግም ይኑር እንጂ እርግማኑስ ብዙ ነው። እያማረሩ ብቻ ከመኖርም እርግማኑን በምርቃት ማርከሱ የተሻለ ነው ባይ ነኝ።

ጋዜጣዊ መግለጫውን የሰጡት ክብርት ነፊሳ እንዲህ ነበር ያሉት፤ “በተቋማችን እንደተሰጠን ኃላፊነት፤ ለኪነ ጥበቡ የምንመኘውን ያህል እንዳንሄድ እንቅፋት የሆነብን ነገር አለ። በሕገ መንግስቱ የተቀመጠለት ሕጋዊ ማዕቀፍ አለመኖሩ ነው። ነገሮችን ለማስፈጸም በተንቀሳቀስን ቁጥር የሚገጥመን እክል ብዙ ነው። ያም ሆኖ የጀመርናቸው ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ለሥራ የሚጠቀሙባቸውን፤ በከባድ ቀረጥ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ቁሳቁሶች ጉዳይ ኪነ ጥበቡን በሚያበረታታ መልኩ እንዲሆን፤ ከሚመለከተው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር በመነጋገር ላይ ነን።

ሁለተኛው ደግሞ እንደ ስፖርቱ ሁሉ ኪነ ጥበብም ከመንግሥት ሠራተኞች ወርሀዊ ደመወዝና ከመሳሰሉት፤ ተቆራጭ የሚደረግ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው እየሠራንበት ነው” በምትለዋ ሀሳብ ላይ፤ ዘርፉ በሁለት እግሩ ቆሞ መሄድ እንዲችል ከራሱ በላይ የሚደርስለት የለምና በሌሎች ሀገሮች እንደምንመለከተው እራሱን ችሎ መንግሥትንም መደገፍ የሚችልበትን የገቢ ምንጭ ለማግኘት መሥራት ይኖርበታል፤ የምትለዋን ጣል አድርገውበታል።

ገና ምናቸውም ያልተነካ አንጡራ የባህልና የኪነት ሀብታት አሉን። በዚህ ውስጥ፤ ለመሥራት ሞክሮ ያበላሸውን ሁሉም በገባው ልክ ተጠያቂ ያደርገዋል፤ ግን ስላልተሠሩትና ስለተረሱትስ ማን ይጠየቅ? . . . ዘርፉን በባለቤትነት የሚይዙ ተቋማት ያስፈልጋሉ። ብዙ ነገሮች ሲበረዙና አይሆኑ ሁነው ሲከስሙ እንመለከታለን፤ እና ማንስ በምን አግባብ ይጠየቃል? ህጋዊ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።

ክብርት ሚኒስትር ዴኤታዋ ”ክብር ለሚገባው ክብርን እንሰጣለን!” ብለውም ነበር። በርግጥም በዚሁ ቃል ከእንግዲህ ወዲያ ብዙ ነገሮች እንደሚለወጡ ተስፋ እናደርጋለን። ካነሳናቸው ነገሮች ባሻገርም፤ እየተሠራባቸው ነው የተባሉ ጉዳዮችም እንዲሁ። እነዚህን ሁሉ ነገሮች ያነሳናቸውም በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋዜጣዊ መግለጫና የሚካሄደውን ዓመታዊውን የ”ክብር ለጥበብ” የዕውቅና ሥነ ሥርዓትን ተንተርሰን እንደመሆኑ፤ ታዲያ ስለ ዕለቱስ የት አለ? ማለታችሁ አይቀርም። ለኛም፤ እንጀራውን አቅርቦ ወጡን መከልከል እንዳይሆንብን፤ ስለ ዕለቱና የዕለቱ አጀቦች፤ በሌላ ጊዜ በሰፊው እናወጋበታለን። ለአሁን፤ ለዛሬው ግን “ክብር ለጥበብ . . . አሜን!!” ብለን እንጨርስ።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የአካል ጉዳተኞች ድምጽ

**እየሩስ ተስፋዬ**




አንዳንድ ቅን ሰዎች አሉ፤ እነርሱ ያሳለፉትን ችግር ሌሎች እንዳይገጥማቸው ሲሉ ልምዳቸውን በተለያየ መንገድ የሚያካፍሉ። በዚህ ሥራቸው እነርሱ በርትተው ሌላውን ያበረታታሉ። ጠንክረው ላልጠነከሩት ብርታት እና አርአያ መሆን ይቻላቸዋል። «አይቻልም» ብለው ተስፋ ለቆረጡትም የ«ይቻላል!!!» መንፈስን በማጋባት የፅናት ምሳሌ እስከመሆን ይደርሳሉ።

ነገሩን ከአካል ጉዳተኞች ጋር ስናያይዘው ደግሞ በርካቶቹ እንደ ጉዳት ዓይነታቸው የተለያዩ ችግሮች እንደሚገጥማቸው እሙን ነው። ከመረጃ እጦት እና ከአመለካከት ጋር የተያያዘ ችግር የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውን ፈታኝ ሲያደርግባቸው ይስተዋላል። ይህን ችግራቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ክፍተቶቻቸውን ለማጥበብ የራሳቸውን ልምድ እና ሌሎች መረጃዎችን በማሰባሰብ የሚሠሩ ግን ጥቂቶች ናቸው።

ኤደን እቋር ትባላለች። ጋዜጠኛ፣ ገጣሚ እና በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ፈጠራ እና መብት ላይ በስፋት ትሠራለች። «ልሳን ለአካል ጉዳተኞች» (Lesan For Disability Organization) የተሰኘ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት መሥራችና ዋና ዳይሬክተር ስትሆን «አካል ጉዳተኝነት እና እርግዝና» የተሰኘ መጽሐፍም ለንባብ አብቅታለች።

ኤደን መጽሐፉን ለመጻፍ ምክንያት የሆናት አካል ጉዳተኞች በመረጃ እጦት በርካታ ችግሮች እንደሚገጥማቸው በማሰብ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ ያለመ ነው። በተለይም አካል ጉዳተኛ ሴቶች በእርግዝና፣ በወሊድና በአራስነት ወቅት የሚያጋጥሙ አብዛኞቹ ችግሮች ቀድመው ቢታወቁ በቀላሉ መታለፍ የሚችሉ መሆናቸውን ከራሷ ልምድ በመነሳት ሌሎች ያለጭንቀት እንዲያልፉት ለማድረግ የድርሻዋን አስተዋጽኦ አበርክታለች።

ኤደን መረጃዎችን ቀድማ አግኝታ ቢሆን ኖሮ ሊያጋጥሟት የሚችሉትን ነገሮች ቀድሞ ለመረዳት እንደሚያስችላት በመግለጽ፤ በተለይም ለሌሎች አካል ጉዳተኛ እህቶቿ ይህንን መጽሐፍ በሚገባ ቀድመው ተረድተው እንዲዘጋጁበት ያግዛል ትላለች። በተጨማሪም ብዙ አካል ጉዳተኛ እናቶች ካላስፈላጊ የሥነ ልቦና እና ተጨማሪ የአካል ጉዳት ሊጠበቁ ይችላሉ ብሎ በማሰብ በጋዜጠኝነት ሙያዋ ስትሠራ ብዙ አካል ጉዳተኞች ከወሊድ ጋር ተያይዞ የገጠማቸውን ችግሮች ጠንቅቃ ታውቃለችና እውቀቷን እና ልምዷን ለማካፈል፤ እንዲሁም ያለውን የግንዛቤ ችግር ለመቅረፍ በሚልም መጽሐፉን እንደፃፈችው ታስረዳለች።

ድርጅቱም ዲጂታል ተደራሽነትን እውን ለማድረግ በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ ከሚያሠራቸው እና ሊሠራቸው ካሰባቸው መካከል መረጃዎችን በስፋት ማዳረስ አንዱ ሲሆን፤ መጽሐፉም http://www.lesanfordisability.org ድረ ገፅ ላይ ይገኛል። አካል ጉዳተኞች የተለያዩ መረጃዎችን እና መጽሐፉን ከድረ-ገጹ በቀላሉ አውርደው ማንበብ እንደሚችሉ ትገልጻለች።

ኤደን እንደምትገልጸው ከሆነ፣ አካል ጉዳተኞችን አስመልክቶ በሚሠራው ሥራ ያለው መተባበር ሰፊ ክፍተት የሚታይበት ነው። ይህንን ለመቅረፍ ሲባል ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን፤ በተለይ በድረ-ገጹ አማካኝነት በርካታ ሥራዎች ይሠራሉ ተብለው ይጠበቃል።

ሌላው ደግሞ አካል ጉዳተኞች ቢቻል ችግር እንዳይገጥማቸው ማድረግ፤ ካልሆነ ግን ችግራቸውን ማቅለል ይገባል። ለዚህ ደግሞ በተቻለ መጠን የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ እና መፍትሔ ላይ በማተኮር የተሻለ ነገር መሥራት እንደሚያስፈልግ ነው የምታስረዳው።

መጽሐፉ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማኅበር ቅርንጫፍ፤ እንዲሁም ካዛንቺስ በሚገኘው የድርጅቱ ቢሮ የሚገኝ ሲሆን፤ ከቅድመ ወሊድ ጀምሮ እስከ አራስነት የሚገጥሙ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ቢታወቁ፣ ቅድመ ዝግጅት ቢደረግባቸው መልካም መሆኑን በመግለፅ ሌሎች አካል ጉዳተኞች እንዲጠቀሙበት መጽሐፉን ከማሳተም በተጨማሪ በነፃ እንዲዳረስ አድርጋለች።

በሕክምናም ይሁኑ ሌሎች ተቋማት ላይ ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። መስማት ለተሳናቸው እና ማየት ለሚቸገሩ ሰዎች የምልክት ቋንቋ የሚችሉ ባለሙያዎች በመቅጠር እንዳይጉላሉ እና እንዳይጨናነቁ ማድረግ ይገባል። እርሷም ሁሉንም መረጃ እና አገልግሎት በተቻለ መጠን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እና አካታች ሆኖ ማየት ምኞቷ እንደሆነ ትናገራለች።


በቀጣይ በርካታ ሥራዎችን ለመሥራት እቅዶች እንዳሏት የምትናገረው ኤደን፤ በተለይም ከዲጂታል ተደራሽነት እና አካል ጉዳተኞችን በጋዜጠኝነት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ከማብቃት፣ መረጃን ተደራሽ ከማድረግ በተጨማሪ በኢኮኖሚ አቅማቸውን ከፍ ከማድረግ አኳያ ሰፊ ሥራዎች ለመሥራት እቅዱ እንዳላት ታስረዳለች።

አካል ጉዳተኞች በእያንዳንዱ አገልግሎት በሚባል ደረጃ በርካታ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። በትራንስፖርት፣ በመንገድ አመቺ አለመሆን፣ የሕንፃ ግንባታዎች ምቹ አለመሆንን ጨምሮ በርካታ ችግሮች እንደሚያጋጥማቸው ይታወቃል። ኤደን እነዚህን ችግሮች ከመዘርዘር እና ትኩረት ከማድረግ ይልቅ በተቻለ መጠን መፍትሔ ላይ አተኩሮ የተሻለ ነገር መሥራት ይገባል ባይ ነች። ለዚያም ነው ዛሬ ላይ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራች ያለችው። ሌሎችም ይህንን ሥራዋን እንድትገፋበት እያበረታቷት ይገኛሉ። እርሷም በሥራዋ ተማምነው ድጋፍ ለሚያደርጉላት እና ለሚያበረታቷት ሁሉ ምስጋናዋን ታቀርባለች።

# ዓለም አቀፍ

## የቀድሞ የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትርና ባለቤታቸው የ14 ዓመት እስር ተፈረደባቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የቀድሞው የፓኪስታን ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካሃን ከባለቤታቸው ጋር የ14 ዓመት እስር ተፈረደባቸው። ካሃን ይህ ፍርድ የተላለፈባቸው በሌላ ወንጀል 10 ዓመት ከተፈረደባቸው ከአንድ ቀን በኋላ ነው።

እ.አ.አ. በ2022 በተቃዋሚዎቻቸው ከሥልጣን የተነሱት ኢምራን ካሃን በአሁኑ ወቅት በሙስና ወንጀል ሦስት ዓመት ተፈርዶባቸው በእስር ላይ ይገኛሉ።

የሀገር ምሥጢር በማውጣት 10 ዓመት ከተፈረደባቸው በኋላ ትናንትና ደግሞ በሙስና ወንጀል 14 ዓመት ተፈርዶባቸዋል። የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የተላለፈባቸውን የእስር ቅጣቶች በተመሳሳይ ጊዜ የሚፈጸሙ ይሆናሉ። የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ግን እነዚህ ክሶች ፖለቲካዊ ናቸው ይላሉ።

ካሃን እነዚህ ቅጣቶች የተላለፉባቸው ሀገራቸው ፓኪስታን ሀገራዊ ምርጫ ለማድረግ አንድ ሳምንት ብቻ ሲቀራት ነው። ካሃን በዚህ ምርጫ እንዳይሳተፉ የታገዱ ሲሆን፣ ፓርቲያቸው ፓኪስታን ቴህሬክ-ኢ-ኢንሳፍ የተለያዩ የምርጫ ቅስቀሳ ገደቦች ተጥለውበታል።

ኢምራን ካሃን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው እያገለገሉ ባሉበት ወቅት ጥንዶቹ የተሰጧቸውን ስጦታዎች ሸጠዋል በሚል የቀረቡባቸውን ክሶች አጣጥለዋል። ካሃን እና ባለቤታቸው ከተላለፉባቸው የእስር ቅጣቶች በተጨማሪ አምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዶላር እንዲከፍሉ ተፈርዶባቸዋል።

የኢምራን ካሃን ፓርቲ ፓኪስታን ቴህሬክ-ኢ-ኢንሳፍ ፍርዱ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ለ10 ዓመታት በምርጫ እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ነው ብሏል።

የፓርቲው ቃል አቀባይ «በፍትሕ ሥርዓታችን ውስጥ አሳዛኙ ቀን» ሲሉ የፍርድ ውሳኔውን ገልጸውታል። ኢምራን ካሃን ሀገራዊ ምሥጢር አውጥተው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን አሻክረዋል ተብለው የተላለፈባቸውን ፍርድ አጥብቀው ተችተዋል።

የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር እና ፓርቲያቸው የቀረቡትን ክሶች «ሐሰተኛ» እንዲሁም ውሳኔውን ያስተላለፈባቸው ፍርድ ቤት የቡድኖችን ፍላጎት እንዲያስፈጽም የተቋቋመ ችሎት ነው ብለውታል።

ቀድሞ ታዋቂ የክሪኬት ስፖርት ተጫዋች የነበሩት ካሃን፣ ደጋፊዎቻቸው ከሳምንት በኋላ በሚደረገው ምርጫ ሰላማዊ መንገድን በመጠቀም ለእያንዳንዱ ኢ-ፍትሐዊ አሠራር ድምጽ በመከልከል እንዲበቀሉ ጠይቀዋል።

## ታጣቂ ቡድኑ አሜሪካ ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት ማቆሙን አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



በዮርዳኖስ ሦስት የአሜሪካ ወታደሮች የተገደሉበትን ጥቃት እንደፈጸመ የተጠረጠረ በኢራቅ የሚገኝ ታጣቂ ቡድን አሜሪካ ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት ማቆሙን አስታወቀ።

ካታይብ ሄዝቦላህ የተባለው ታጣቂ ቡድን ለዚህ ውሳኔው ምክንያቱን ሲገልጽ «የኢራቅ መንግሥት ሊደርስበት የሚችለውን አሳፋሪ ምላሽ ለመከላከል ነው» ብሏል።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ባለፈው እሁድ በዮርዳኖስ የሚገኘው የአሜሪካ የጦር ሰፈር ላይ ለተፈጸመው እና ለሦስት ወታደሮች ሞት ምክንያት ለሆነው ጥቃት አጸፋዊ ምላሽ የሚሰጥበትን መንገድ መወሰናቸውን ገልጸዋ«ል። አሜሪካ በተደጋጋሚ የአጸፋ ምላሹ ወታደራዊ ጥቃት ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ ሰጥታለች።

ከእሁዱ ጥቃት ጀርባ ነበርኩ ያለው ካታይብ ሄዝቦላህ የጸጥታ ዘርፍ ዋና ጸሐፊ አቡ ሁሴን አል ሃሚዳዊ ባወጣው መግለጫ «በኢራቅ መንግሥት ላይ የሚደርሰውን አሳፋሪ ምላሽ ለመከላከል በሚል ወራሪ ኃይሎች ላይ የምንወስደውን እርምጃ ብናቋርጥም በጋዛ ሕዝባችንን መከላከል እንቀጥላለን» ብሏል።

ባለፈው እሁድ በዮርዳኖስ እና ሶሪያ ድንበር አካባቢ የተፈጸመው ጥቃት በኢራን ሠራሽ ድሮን እንደሆነ ተዘግቧል። በዚህ ጥቃት ሦስት ወታደሮች ከመገደላቸው በተጨማሪ በርካታ የአሜሪካ ወታደሮችም ጉዳት ደርሶባቸዋል።

አሜሪካ ይህንን ጥቃት የፈጸሙት በኢራን የሚደገፉ ኃይሎች ናቸው ብትልም ካታይብ ሄዝቦላህ የጥቃቱ ፈጻሚ ነው ብላ አልደመደመችም።

ታጣቂ ቡድኑ አሜሪካ ላይ ጥቃት መሰንዘሬን አቁሜያለሁ ማለቱን ተከትሎ የፔንታገን ቃል አቀባይ በሰጡት መግለጫ «ድርጊት ከቃል በላይ ይናገራል» ሲሉ ተደምጠዋል።

ቃል አቀባዩ ፓት ራይደር አክለውም ድርጊቱ ከባድ መዘዝ እንደሚያስከትልም አክለዋል። አሜሪካ ጥቃት የደረሰበት እና በዮርዳኖስ የሚገኘውን የጦር ሰፈር ጥበቃ እያጠናከረች ትገኛለች።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ግብጽ ግን የት ነበረች…!?

ታሪካዊና ፖለቲካዊ ነፍስ ካወቅሁበት ጊዜ አንስቶ ሁል ጊዜ እንደ እግር እሳት የሚለበልበኝ፤ እ-ህ-ህ የሚያስብለኝና የሚያቃትተኝ የኤርትራ ከኢትዮጵያ መነጠልና ቀይ ባሕር ላይ ያለንን ስፍራ ማጣታችን ነው። ቀይ ባሕርን ማጣቱ እንደ ሀገርና ሕዝብ ብቻ ሳይሆን እንደ ግለሰብ በየዕለቱ መራቆት እንዲሰማኝ አድርጓል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዚህ ማጣት በዳረጉን ላይ ዛሬ ድረስ ከንፈሬን እየነከስሁ አለሁ። ምን አለፋችሁ በማላውቀው ምክንያት ስሜቱ ፐርሰናል ነው። ጥንታዊና ታሪካዊ ከሆነው የሀገራችን ስንክሳር ዋናው ምዕራፍ ተገንጥሎ የወጣ ያህል ይሰማኛል። ቀይ ባሕር ከወደብና ከባሕር በር በላይ ነው። የታሪካችን፣ የስልጣኔያችንና የማንነታችን መግቢያ በር ነው። የገዘፈ ጂኦፖለቲካዊ አንድምታና በምንም የማይለካ ስትራቴጂካዊ ዋጋ ያለውን ባሕር በተቀነባበረ ሴራ እንድናጣው ሆኗል።

ይህን ወሳኝ የሀገራችንን ክፍል እንድናጣ ታሪካዊ ጠላታችን ግብፅ የአንበሳውን ድርሻ ተጫውታለች። የእሷ ሳያንስ የአረቡን ዓለም በማስተባበር ከአማጽያኑ ጎን እንዲቆሙ በማድረግ ሀገራችን ለተራዘመ፣ ዘግናኝና አውዳሚ ለሆነ የእርስ በርስ ጦርነት ተዳርጋ ቆይታለች። ደርግ በትጥቅ ትግል ከተገረሰሰ፣ ኤርትራም ከተገነጠለች በኋላ ደግሞ ሀገራችን በማንነትና በልዩነት ላይ የተመሠረተ ርዕዮተ ዓለም እንድትከተል ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ የተከፋፈለችና የተዳከመች ሀገር ሆና እንድትኖር ግብጽ ተደጋጋሚ ደባ ፈጽማለች። ዛሬም ያለንበት ሁኔታ አልበቃ ብሏት አልተኛችልንም።

በታሪክና በጅኦፖለቲካዊ አጋጣሚ ያገኘችውን ተጽዕኖ በመጠቀም ለዓመታት ወንዞቻችንን አልምተን እንዳንጠቀም ከዓለማቀፍ የገንዘብ ተቋማት ብድር እንዳናገኝ ስታሻጥር ኖራለች። በራሳችን አቅም ታላቁን የሕዳሴ ግድብ ለመገንባት ስንነሳ ለማጨናገፍ ያልፈነቀለችው የዲፕሎማሲና የሴራ ድንጋይ የለም። አራተኛው የውሃ ሙሊት በተቀመጠለት ዕቅድ መከናወኑና አጠቃላይ የግድቡ ግንባታም ወደ 95 በመቶ መጠጋቱ፤ ኢትዮጵያ የአሁኑንም ሆነ የወደፊት ትውልዷን በዓባይ ውኃ የመጠቀም መብት አሳልፋ እንደማትሰጥ በተግባር መረጋገጡ ግብጽን የቆሰለ አውሬ አድርጓታል። ሰሞነኛ አኳኋኗ ይሄን የሚያሳይ ነው።

ግብፅ አባይን ከምንጩ ለመቆጣጠር፣ ሀገራችንን ቅኝ ለመግዛት፣ ጠንካራ ሉዓላዊ ሀገር ሆና እንዳትወጣና የውሃ ሀብቷን አልምታ እንዳትጠቀም፤ አባይ የሚገደብበት ቀን እውን እንዳይሆን ከደርዘን ጊዜ በላይ ወራናለች። በስውር ደግሞ ምን አልባት ከሺህ ጊዜ በላይ ከጀርባ ወግታናለች። በተለይ ከ20ኛው መክዘ ወዲህ ደግሞ በተለያዩ የውስጥና የውጪ ሀይሎች የውክልና (proxy) ጦርነት በማካሄድ ሀገራችንን ስታደማ ኖራለች። ይህ እኩይ ሴራዋ ከሞላ ጎደል በመሳካቱ አሳንሳ ቁልቁል ስታየን ኖራለች። ከታሪካዊዋ ሀምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ግን ማለትም የመጀመሪያው የሕዳሴው የውሃ ሙሊት በስኬት ከተጠናቀቀ በኋላ ግን ሁኔታዎች ተቀይረዋል።

በሴራና በደባ በቀጣናውም ሆነ በዓለማቀፍ መድረክ ያሳጣችውን ጂኦ ፖለቲካዊ እና ስትራቴጂካዊ ስፍራ ከ32 ዓመታት በኋላ መልሰን ተረክበናል። ምርኳችን ተመልሷል። የቀጣናው ጂኦ ፖለቲካዊ አሰላለፍ በታላቁ የህዳሴ ግድብ እንደ አዲስ ተበይኗል። ተፐውዟል። ከዚህ በኋላ የሀገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ጂኦ ፖለቲካዊ ስፍራ ከ1983 ዓ.ም በፊት ወደነበረው ከመመለሱ ባሻገር ከግብፅ የሚተናነስ አይደለም። በዚህ ከፉኛ የተቆጣችው ግብጽ የሴራ ወጥመዷን አጥምዳ ስትጠብቅ በእኛ ታህሳስ 22 ቀን 2016 ዓ.ም በነጮች ጥር 1 ቀን 2024 ዓ.ም በህልሟም ሆነ በእውኗ ይሆናል ብላ ያልገመተችው ክስተት ተፈጠረ። በልበ ሙሉነት ከ30 ዓመት በፊት ዘግቸዋለሁ ያለችው የባሕር በር ፋይል እንደ አዲስ ተከፈተ። ሀገራችን የባሕር በር ለማግኘት ጥርጊያ መንገዱን የሚያበጅ የመግባቢያ ሰነድ ከሱማሌላንድ ጋር ተፈራረመች።

እውነት ለመናገር ይህ ለግብጽ ያልተጠበቀ እና አስደንጋጭ መርዶ መሆኑን ለመረዳት ሞራ ገላጭ መሆን አያሻም። ስምምነቱ እውን የሚሆን ከሆነ ኢትዮጵያ የባሕር በር በማግኘት በቀጣናው የሚኖራት ጅኦፖለቲካዊ ስፍራ ከፍ ሊል ነው። ይህ ደግሞ ለግብጽ በፍጹም የሚዋጥ አይደለም። ለዚህ ነው ተሯሩጣ ስምምነቱን በአረብ ሊግ ከማስወገዝ አልፋ የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ግብጽን እንዲጎበኙ ኦፊሴላዊ የግብዣ ጥሪ ያደረገችው። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯንም ወደ አስመራ የላከችው። ኢጋድም በጉዳዩ ላይ እንዲነጋገር ከጀርባ ሆና ዲፕሎማሲያዊ እና ፖለቲካዊ ድጋፍ ያደረገችው።

መች በዚህ ልታቆም የጸጥታው ምክር ቤት በኢትዮጵያና በሶማሊላንድ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ዙሪያም ስብሰባ እንዲጠራ አድርጋለች። በመንግስቷ እና በአረብ ሊግ አማካኝነት ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር ያደረገችው ስምምነት የተመድን ቻርተር ጥሷል በሚል ምክር ቤቱ ስብሰባ እንዲቀመጥ ባመለከተችው መሠረት የወሩ የምክርቤቱ ሰብሳቢ ፈረንሳይ በጠራችው በዚህ ስብሰባ፤ በኢትዮጵያና በሱማሊያ ውዝግብ ላይ መክሯል።

ከምክር ቤቱ ስብሰባ ቀደም ብሎ የምክር ቤቱ የወቅቱ ሊቀመንበር ፈረንሳይ፣ አፍሪካውያኑን የምክር ቤቱ ተለዋጭ አባላት አልጀሪያን፣ ሞዛምቢክንና ሴራሊዮንን እንዲሁም ጉያናን በጉዳዩ ዙሪያ በዝርዝር ያማከረች ሲኾን፣ አራቱ አገራትም ኢትዮጵያንና ሱማሊያን ማነጋገራቸው ተገልጧል። ዓረብ ሊግና የእስልምና አገራት ካውንስል፣ የሱማሊያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት እንዲከበር ለጸጥታው ምክር ቤት ቀደም ሲል ደብዳቤ አስገብተው ነበር። ከዓረብ አገራት መካከል፣ የጸጥታው ምክር ቤት አባል የኾነችው አልጀሪያ ብቻ ናት። የስብሰባው ውጤት ይህን መጣጥፍ እስካጠናቀርሁበት ሰዓት ድረስ አልተገለጠም።

ከሁሉም የሚያስገርመው ላለፉት 30ና ከዚያ በላይ ዓመታት ሶማሊያ አንድ ጊዜ በአልቃይዳ ሌላ ጊዜ በእስላሚክ ኮርት አሁን ደግሞ በአልሻባብ እንደ ሀገር መቆም ተስኗት እየተፍገመገመች የት ወደቀሽ ብላት የማታውቅ ግብጽ ለሶማሊያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ተቆርቋሪ ሆና ብቅ ብላለች። እስከ ዛሬ የት ኑራ ነው ዛሬ ያዙኝ ልቀቁኝ የምትለው። እውነት ለሉዓላዊነት ቃፊር ብትሆን ኖሮ አፍንጫዋ ስር ሀገርና ፓስፖርት አልባ ለሆኑት ፍልስጤማውያን ድምጽ በሆነች። እሷ ግን በአደራዳሪነት ስም በሁለት ቢለዋ ከአረቦችም ከምዕራባውያን እየበላች ነው።

ይህ እንዲቀርባት ስለማትፈልግ የፍልስጤም ጉዳይ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ አትሻም። የጎረቤቷን የሱዳን ችግር ከመፍታት ይልቅ ጎራ ለይታ እየደገፈች ሱዳንን እያፈረሰች፣ ምስራቅ አፍሪካን እያተራመሰች ትገኛለች። በዚህ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት በፈጠርነው ክፍተት ግብጽ ሽብልቅ ሆና ልዩነትን ለማስፋት የሄደችበት ርቀት ቢያስተዛዝብም፤ ኢትዮጵያና ሶማሊያ በሊግ (በአረብ ሊግ) ሳይሆን በደም የተሳሰሩ ሕዝቦች ስለሆኑ የተፈጠረው አለመግባባት በመነጋገር ይፈታል። ግብጽም በስራዋ ታፍራለች።

የጨረተ Clichy ግን ደግሞ ዛሬም በየአጋጣሚው ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ ባለ 24 ካራት የነጮች ወርቅ ይትበሀል አለ። "ጎደኞችህን መርጠህ መጎዳኘት ትችላለህ። ጎረቤትህን ግን መርጠህ ጎረቤት ማድረግ አትችልም። "/"You can choose your friends, but you can't choose your family."/አዎ ሀገራችን ከሱዳን፣ ከኤርትራ፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከጅቡቲ፣ ከኬኒያና ከሶማሊያ ጋር ጎረቤት የሆነችው መርጣና ፈቅዳ አይደለም። ከግብጽ ጋር አንድ ወንዝ የምትጠጣውም መርጣና ፈቅዳ ባይሆንም በእሱ የተነሳ ብዙ ዋጋ ከፍለናል። እየከፈልንም እንገኛለን። ይህ ተፈጥሮአዊ እጣ ፈንታ ሀገራችንን ወዳጅ ሊያደርጋት ሲገባ ከዘፍጥረት እስከ ሀዲስ ዋጋ እያስከፈላት ነው። አበው እማው ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ዘላለም ሲያለቅስ ይኖራል እንዲሉ።

የግብጹ ፕሬዚዳንት አብዱል ፈታህ አል ሲሲ፣ ግብጽ ማንም በሱማሊያ ላይ ስጋት እንዲደቅንባት ወይም ብሔራዊ ደኅንነቷን እንዲጎዳ አትፈቅድም ሲሉ በዚያ ሰሞን ከሱማሊያው ፕሬዚዳንት ሐሰን ሞሃመድ ጋር ካይሮ ውስጥ በሰጡት መግለጫ ተናግረዋል። ሲሲ፣ ሱማሊያ የዓረብ ሊግ አባል በመኾኗ ኹሉም የሊጉ አባላት ከጥቃት ይጠብቋታል ብለዋል። ግብጽም ሆኑ የአረብ ሊግ አባላት መጀመሪያ ቀይ ባሕርን ከህውቲ ሚሊሻዎች ጥቃት በተከላከሉ። "ወንድሞቻችን በተለይ ጣልቃ እንድንገባ ከጠየቁን ባትፈትኑን ይሻላል" ያሉት ሲሲ፣ አንድን መሬት ለመቆጣጠር ማሰብ ማንም ሊቀበለው እንደማይችል ለኢትዮጵያ መልዕክት ማስተላለፍ እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። ፈተና ከተባለስ ታላቁን የሕዳሴ ግድብ ከመገደብ በላይ ምን ፈተና ነበር። ሲሲ፣ ከኢትዮጵያና ሶማሊላንድ የባሕር በር ስምምነት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ላይ ዛቻ አዘል መልዕክት ሲያስተላልፉ የትናንቱ የመጀመሪያቸው ነው።

ራስ ገዟ ሶማሊላንድ ከኢትዮጵያ ጋር ከተፈራረመችው የባሕር በር የመግባቢያ ስምምነት ጋር በተያያዘ ማናቸውንም የውጭ ጣልቃ ገብነት እንደምትቃወም አስታውቃለች። ሶማሊላንድ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴሯ በኩል ሰሞኑን ባወጣችው መግለጫ፣ ግብጽ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቷን እንደ ሱዳን፣ ሊቢያና ጋዛ በመሳሰሉ ግጭቶች ባሉባቸው ጎረቤቶቿ ላይ ብታውለው ይሻላታል ስትል መክራለች። ቀጠናዊ ጉዳዮችን በንግግርና ትብብር ለመፍታት ቁርጠኛ መኾኗን የጠቀሰችው ሶማሊላንድ፤ በቀጠናው ሰላምና ልማት ለማምጣት ከኹሉም አገራት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ውይይቶችንና ትብብሮችን እንደምታደርግ ገልጣለች። ለግብጽ ዛቻ ኢትዮጵያ ብዙም ቁብ የሰጠችው ባይመስልም በተፈጠረው ጉዳይ ላይ ግን ለመነጋገር ዝግጁ መሆኗን ደጋግማ ገልጣለች። ግብጽን ወደ አንዘረዘራት የጂኦፖለቲካ ጉዳይ እንመለስ።

ሀገራችን በቀጣናው ያላትን ጂኦ ፖለቲካዊ ሞገሷን ላለፉት 32 ዓመታት ተነጥቃ ኖራለች። የኢትዮጵያ ሕዝብና የለውጡ አመራር ግድቡ ከለየለት ክሽፈት ድኖ ዛሬ ላይ አፈጻጸሙ 95 በመቶ ደርሷል። 540 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይልም ማመንጨት ችሏል። አራተኛው ዙር ውሃ ሙሊትም ተጠናቋል። ከሁሉም ከሁሉም በላይ ግን እንደ ቬኒዞላ ገንዘብ "ቦሊቫር" ጋሽቦ የነበረውን የሀገራችንን ስትራቴጂካዊ ይዞታ ወይም ጅኦፖለቲካዊ ስፍራ በሕዳሴው ደንደስ መመለስ ተችሏል።

ቀለል ባለ አገላለጽ ጂኦፖለቲክስ ማለት ከአለማቀፍ ግንኙነት አንጻር ወይም አኳይ የጅኦግራፊንና የፖለቲካን ግንኙነት ማጥናት ነው። የሀገራችን ድንበር፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የሕዝብ አሰፋፈር፣ የእድገት ደረጃ፣ የምታራምደው የፖለቲካ ስርዓትና ወታደራዊ አቅም የሀገራችንን የጅኦፖለቲክስ ይወስናል። የሀገራችን የሕዝብ ብዛትና የተፈጥሮ ሀብት ጅኦፖለቲክሷን ከፍ ሲያደርጉት በአንጻሩ የሀገሪቷ ውስጣዊ አንድነት ደካማ መሆን ጅኦፖለቲካዊ ስፍራዋን ወይም ዋጋውን ያሳንሰዋል። የሕዳሴው ግድብ መጠናቀቅ ደግሞ ጅኦፖለቲካዊ ቦታዋን ከፍ ያደርገዋል።

የአረቡ ዓለም የነዳጅ ባለቤት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ እኤአ በ1948 ዓ.ም እስራኤል የአይሁዶች መንግስት ሆና ከቆመች፣ ከ1993 ዓ.ም የመስከረም 1 ቀን የሽብር ጥቃት በኋላ የአሜሪካ፣ የምዕራባውያንና የዓለማቀፉ ተቋማት የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ማጠንጠኛ ነዳጅ ፣ የእስራኤል ደህንነት እና የጸረ ሽብር ዘመቻ ሆነ። ዛሬ እንዲህ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ወደ ቻይናና ራሽያ ሊወሰድ። ሆኖም ለቆየው የአሜሪካ የውጭ ግንኙነት ፖሊስ እና ስትራቴጂ ተግባራዊነት ከአረቡ ዓለም ግብፅ ቀዳሚዋ ስትራቴጂካዊ አጋር ሆና ተመርጣለች። ግብፅን ተመራጭ ያደረጋት ለምዕራባውያን የጡት ልጅ እስራኤል ጎረቤት መሆኗ፤ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጧ በተለይ የስዊዝ ቦይ ባለቤት መሆኗ፤ የእስላማዊ ትምህርት ማዕከል እና የአረብ ብሔርተኝነት አቀንቃኝ መሆኗ፤ ዜጎቿ ከሌላው የአረብ ዓለም ጋር ሲነጻጸር በዓለማዊም ሆነ በእስላማዊ ትምህርት የገፉ በመሆናቸው በአጠቃላይ በነበራት ጂኦፖለቲካዊ በምዕራባውያንም ሆነ በእስላማዊው ዓለም ዘንድ ሞገስ አግኝታለች።

ይህን ሞገሷን የአረቡን ዓለም ጨምሮ የአረብ ሊግን እንዳሻት ለማሽከርከር ትጠቀምበታለች። በልዩነትና በክፍፍል ከሚንጠራወዘው የአረቡ ዓለም ግብፅ እንደ ሰንደቅ ከፍ ብላ እንድትታይ ረድቷታል። ይህን መከፋፈል እስራኤልን ጨምሮ አሜሪካውያን ሆኑ ምዕራባውያን ይፋ ባያወጡትም የሚደግፉት ስለሆነ ግብፅ ሽብልቅ ሆና እንድታገለግል አሞሌ እያላሱ (ብድርና እርዳታ እየሰጡ በአናቱ የጦር መሳሪያ እስካፍንጫዋ እያስታጠቁና ወታደራዊ ስልጠና እየሰጡ ይንከባከቧታል። ይጎበኟታል። አሜሪካ ብቻ በየዓመቱ ወደ 4 ቢሊየን ዶላር የሚጠጋ የጦር መሳሪያ ፣ የወታደራዊ እርዳታና የልማት ድጋፍ ታደርጋለች ።

ግብፅ በአጠፋው ይህን ውለታ ከግምት ያስገባ እና እኤአ በ1979 በአንዋር ሳዳትና በእስራኤል መካከል የተፈረመውን የሰላም ስምምነት መሰረት ያደረገ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀርጻለች። የሀገሪቱን ኢኮኖሚ፣ ደህንነትና ፖለቲካ በመዳፉ የጠቀለለው የግብፅ ጦርና ደህንነት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል በአይነ ቁራኛ ይከታተላል። ዘብ ሆኖ ሌት ተቀን ከአረቡ አብዮት በኋላ በምርጫ የፈርኦኖችን በትረ ስልጣን ጨብጠው የነበሩ የመጀመሪያው የእስላም ወድማማቾቹ አባል ፕሬዚዳንት ሞሐመድ ሙርሲ እንኳ የድርጅታቸውንም ሆነ አክራሪ እስላሞች ግፊት ተቋቁመው የግብፅና እስራኤልን የሰላም ስምምነት ማክበር ችለዋል ።

መጀመሪያ በመፈንቅለ መንግስት በኋላ በምርጫ ወደ መንበሩ የመጡት ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲም ከሳዳት ፣ ከሙባረክና ከሙርሲ በላይ የሰላም ስምምነቱን እያስፈጸሙ ነው ። የእስራኤል ጉዳይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ቀኖና ነው ማለት ይቻላል ። ከእስራኤል ጀርባ ደግሞ አሜሪካ አለች ። ግብፅ ናይል የሕልውናዬ ጉዳይ ነው ብላ በሕገ መንግስቷ ብታካትተውም ፤ በውስጠ ታዋቂ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ የማዕዘን ራስ ቢሆንም በግላጭ ትኩረቱ እስራኤል ፣ ፍልስጤምና አሜሪካ ላይ ነው ።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት





## ድምቀት የገደለው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና

ብርሃን ፈይሳ



የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከሚያዘጋጃቸው ውድድሮች መካከል ትልቁ የሆነው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና በ1963 ዓ.ም ነበር የተጀመረው። ውድድሩ ሀገርን በዓለም አቀፍ ደረጃ መወከል የቻሉ አትሌቶችን ማፍራት ዋነኛ ዓላማው ሲሆን፤ አንጋፋዎቹን አትሌቶች እነ ሻምበል ምሩጽ ይፍጠርን ጨምሮ አሁን በውድድር ላይ እስካሉት ወጣት አትሌቶች ድረስ በርካቶችን አፍርቷል። ዘንድሮ ለ53ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በመካሄድ ላይ ያለው ይህ ዓመታዊ ቻምፒዮና አዋቂ እና ተተኪ አትሌቶችን እያፎካከረም ይገኛል።

ከአጭር እስከ ረጅም ርቀት የመም ሩጫ፣ የውርወራ እና ዝላይ ስፖርቶች በሚያካትተው ውድድሩ 5 ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፤ እንዲሁም 27 ክለቦች 1ሺህ 102 የሚሆኑ አትሌቶቻቸውን እያሳተፉ ነው። በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከላት እና አካዳሚ የሚሠለጥኑ ተተኪና ወጣት አትሌቶችም አቅማቸውን የሚለኩበትን እና ሀገራቸውን የሚወክሉበትን ዕድል የሚያስገኝላቸው ውድድርም ነው። በመሆኑም ክለቦችና የማሠልጠኛ ተቋማቱ ትኩረት ሰጥተው በዓመታዊ የውድድር መርሃ ግብራቸው የሚያስቀድሙት ነው።

ከትናንት በስቲያ የተጀመረው ቻምፒዮናው በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ክቡር አቶ ቀጀላ መርዳሳ፣ የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ አቶ ዳዊት አስፋው፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ አትሌቶች እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተዋል። ውድድሩ በዓለም አቀፍ ቻምፒዮና ደረጃ መሠረት የመክፈቻና መዝጊያ መርሐ ግብሩ ከሰዓት በኋላ የሚደረግ ሲሆን፤ በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ለአትሌቲክስ ቤተሰቡ ሊደርስ ችሏል። ሆኖም ከዚህ ቀደም ይህ ቻምፒዮና ከዚህ ቀደም ይካሄድበት ከነበረው ድምቀት በእጥፍ ባነሰ ሁኔታ መቀጠሉን ለመታዘብ ይቻላል። የኢትዮጵያ ቻምፒዮና በርካታ ደጋፊዎች በተገኙበት ይካሄድ የነበረው በአትሌቶች መካከል በነበረው እልህ አስጨራሽና እጅግ ጠንካራ የፉክክር ስሜት ነበር። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ውድድሩ የተለመደው ድምቀቱ እምብዛም እየታየበት አለመሆኑ የስፖርት ቤተሰቡ የሚስማማበት ነው።

በእርግጥ ቻምፒዮናው ለዓመታት ይካሄድ የነበረው በአንጋፋው የአዲስ አበባ ስታዲየም በመሆኑ ለደጋፊዎችና የአትሌቲክስ ወዳጆች ለመታደም ምቹ ነበር። ስታዲየሙ ከእድሳት ጋር በተያያዘ ውድድሮችን የማያስተናግድ መሆኑ ቻምፒዮናው በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ መም ላይ ለማካሄድ አስገዳጅ በመሆኑ የተመልካቹም ቁጥር ሊቀንስ መቻሉ እሙን ነው። እንደ ሀገር ስፖርቱ እያለፈባቸው ከሚገኙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች መካከል የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አለመኖር ቀዳሚው ነው። ይህንን ሁኔታ በተለይ እየተጋፈጡ ከሚገኙ ስፖርቶች መካከል አንዱ አትሌቲክስ ሲሆን፤ በዚህ የተነሳም ቻምፒዮናውን በአካዳሚው የመለማመጃ መም የውርወራ ስፖርቶችን ደግሞ ሱሉልታ በሚገኘው የቀነኒሳ በቀለ የአትሌቲክስ ማዘውተሪያ እየተካሄደ ይገኛል።

ነገር ግን የውድድሩ ድምቀት ለመደብዘዙ ይህ ብቻውን ምክንያት ሊሆን አይችልም። ይልቁኑ በተወዳዳሪዎች መካከል ያለው የፉክክር መንፈስ እና አቅምንም የሚያካትት ነው። ክለቦችና ማሠልጠኛ ተቋማቱ ከዓመት ዓመት ‹‹ባለህበት እርገጥ›› የሆነ አካሄድ መከተላቸው በአትሌቶች አቅም ላይ አሁንም መልስ ሊገኝለት ያልቻለው ጉድለት እንዲቀጥል ምክንያት በመሆኑ ውድድሩን ሳቢ ሊያደርገው አልቻለም። ከዘመኑ ጋር ሊዘምኑ ያልቻሉ ክለቦችና ማሰልጠኛ ተቋማቱ በሥልጠና እና የስፖርት ቁሳቁስ ማነስ ለውድድር ብቁ ያልሆኑ አትሌቶችን እያፈሩ መቀጠላቸውን ከውድድሩ መታዘብ ይቻላል። ለአብነት ያህል የውድድር ማስጀመሪያ ሕግን ባለማወቅ ከውድድር ውጪ የሚሆኑ፣ በሜዳ ተግባራት ደግሞ መሣሪያዎቹን በትክክል ለመጠቀም ባለባቸው የልምድ ማነስ ዕድላቸውን የሚያበላሹ አትሌቶችን ማንሳትም ይቻላል።

በቀጣዩ ወር በጋና/አክራ በሚካሄደው 13ኛው የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች ላይ ኢትዮጵያ ከአጭር ርቀት እስከ ሜዳ ተግባራት ለመሳተፍ ዕቅድ አላት። በመሆኑም መሰል አትሌቶችን ማሰለፍ ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል አስቀድሞ መመልከት ያሻል። ክለቦች ከጊዜው ጋር ለመራመድ ያላቸው እንቅስቃሴ ከማነሱ ባለፈ ፌዴሬሽኑም ውድድሩ ላይ ከወትሮ ያልተለየ አካሄድ መከተሉም ሊነሳ የሚችል ጉድለት ነው። ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ተመሳሳይ ውድድር በተመሳሳይ ሁኔታ ማካሄድ ተሳታፊዎች እንዳይነቃቁ ማድረጉ አልቀረም። በመሆኑም ፌዴሬሽኑ አስገዳጅ መመሪያዎችን በማውጣት፤ እንዲሁም ግንዛቤ በማስጨበጥ ውድድሩ የወትሮ ድምቀቱን እንዲያገኝ ሊተጋ ይገባል።